# ትንቢተ ዘካርያስ

## መግቢያ

### ታሪካዊ ዳራው

ዘካርያስ የትንቢት አገልግሎት የሰጠው ከምርኮ ዘመን በኋላ ሲሆን፣ አይሁድ ከባቢሎን ምርኮ በተመለሱበት ጊዜ ነበር፤ ዝርዝር ታሪኩን በሚገባ ለመረዳት ከትንቢተ ሐጌ መግቢያ ላይ "ታሪካዊ ዳራው" የሚለውን ይመ::

### ጸሐፊውና የጽሑፉ ወጥነት

ኤርምያስ (1፥1) እና ሕዝቅኤል (1፥3) ነቢይ ብቻ ሳይሆኑ ካህንም እንደ ነበሩ ሁሉ፣ ዘካርያስም ነቢይና ካህን ነበር (1፥1):: ዘካርያስ የተወለደው በባቢሎን ሲሆን፣ በዘሩባቤልና በኢያሱ መሪነት በ538 ዓ.ቅ.ክ ወደ ይሁዳ ከተመለሱት ሰዎች መካከል አንዱ ነበር:: በነህ 12፥4 ላይ አያቱ አዶ ከምርኮ ከተመለሱት ሰዎች ዝርዝር ውስጥ ተጠቅሶአል:: በኋላም ኢዮአቄም ሊቀ ካህን በነበረበት ጊዜ፣ ዘካርያስ ከካህናት ወገን ለነበሩት አለቃ በመሆን (ነህ 12፥10-16) አዶን ተክቶአል (1፥1 :7)፤ ዘካርያስ የአያቱን ቦታ ሊይዝ የቻለው አባትየው (በራክዩ፣ 1፥1 :7) በወጣትነቱ ስለ ሞተ ነው የሚል ግምት አለ::

ዘካርያስ የነበረው ሐጌ በነበረበት ዘመን ነው (ዕዝ 5፥1፤ 6፥14)፤ ነገር ግን ከእርሱም በኋላ ለብዙ ጊዜ አገልግሎአል (1፥1 እና 7፥1 ከሐጌ 1፥1 ጋር ያነጻጽሩ፤ ነህ 12፥1-16 ማብ ይመ):: በወጣትነት ዕድሜው አገልግሎት በመጀመሩ (2፥4 ይመ)፣ እስከ ቀዳማዊ አርጤክስስ ዘመነ መንግሥት (465-424 ዓ.ቅ.ክ) ድረስ ቈይቶ ሊያገለግል ችሎአል::

በስሙ የተጠራውን ይህን መጽሐፍ ዘካርያስ ሙሉ በሙሉ ሳይጽፍ አይቀርም:: አንዳንድ ምሁራን ከም 1-8 ያለውን ክፍል የጻፈው ጸሐፊ ከም9-14 ያለውን ከጻፈው እንደሚለይ በማገለጽ የተጻፈበትን ስልትና የቅንብር ይዘቱን፣ እንዲሁም ታሪካዊ ሁነቶችንና የዘመን አቈጣጠር በማስረጃነት ያቀርባሉ:: ዘካርያስ የመጽሐፉ ጸሐፊ አለመሆኑን ለማገለጽ የቀረበው ይህ ተቃውሞ አጥጋቢ አይደለም፤ የመጽሐፉንም ወጥነት አጠራጣሪ ሊያደርግ አይችልም::

### የተጻፈበት ጊዜ

የዘካርያስ መልእክት የተጻፈበት ጊዜ ከሐጌና ከሌሎች ታሪካዊ ድርጊቶች ጋር የተያያዘ ነው:: ከዚህ በታች እንደተመለከተው፤

1) የመጀመሪያው የሐጌ መልእክት (ሐጌ 1፥1፤ ዕዝ 5፥1)፣ በ520 ዓ.ቅ.ክ
2) የቤተ መቅደሱ እንደ ገና መሠራት መጀመር (ሐጌ 1፥12-15፤ ዕዝ 5፥2)፣ በ520 ዓ.ቅ.ክ
   - የቤተ መቅደሱ ሥራ መስተጓጐል (ዕዝ 4፥1-5)፣ ከ536-530 ዓ.ቅ.ክ
   - የሥራው ፈጽሞ መቆም (ሐጌ 2፥1-9)፣ ከ530-520 ዓ.ቅ.ክ
3) ሁለተኛው የሐጌ መልእክት (ሐጌ 2፥1-9)፣ በ520 ዓ.ቅ.ክ
4) የዘካርያስ ስብከት መጀመሪያ (1፥1-6)፣ በ520 ዓ.ቅ.ክ
5) ሦስተኛው የሐጌ መልእክት (ሐጌ 2፥10-19)፣ በ520 ዓ.ቅ.ክ
6) አራተኛው የሐጌ መልእክት (ሐጌ 2፥20-23)፣ በ520 ዓ.ቅ.ክ
7) የቤተ መቅደሱ እንደ ገና መሠራት አስመልክቶ የተንተናይ ደብዳቤ ለዳርዮስ (ዕዝ 5፥3-6፥14) 519-ከ518 ዓ.ቅ.ክ

- ቤተ መቅደሱ እንደ ገና መሠራት በመጀመሩና በተንትናይ መምጣት መካከል የጊዜ ክፍተት አለ::

8) የዘካርያስ ስምንቱ ራእዮች (ም 1፥7-6፥8)፣ በ519 ዓ.ቅ.ክ
9) ኢያሱ አክሊል መድፋቱ (ም 6፥9-15)፣ በ519 ዓ.ቅ.ክ
10) የንስሓ ጥሪና የበረከት ተስፋ (ም 7-8)፣ በ518 ዓ.ቅ.ክ
11) የቤተ መቅደሱ መመረቅ (ዕዝ 6፥15-18)፣ በ516 ዓ.ቅ.ክ
12) የዘካርያስ የመጨረሻ ትንቢት (ም 9-14)፣ ከ480 ዓ.ቅ.ክ በኋላ

### የተጻፈበት ምክንያትና ዐላማው

ትንቢተ ዘካርያስ የተጻፈበት ምክንያት ከትንቢተ ሐጌ ጋር ይመሳሰላል (ከሐጌ ታሪካዊ ዳራ "የተጻፈበት ጊዜ" የሚለውን ይመ):: ዘካርያስና ሐጌ መንፈሳዊ ተሐድሶ እንዲመጣ የሚፈልጉ ቢሆንም የሁለቱም ነቢያት ዋና ዐላማ የይሁዳን ሕዝብ መገሠጽና የጀመሩትን የቤተ መቅደሱን ሥራ እንዲጨርሱ ማደፋፈር ነበር (4፥8-10 ፤ ሐጌ 1፥2)፤ እንዲሁም በ1፥7-6፥8 ላይ የተጠቀሱት የሳምንቱ የሌሊት ራእዮች ዐላማ ምን እንደ ሆነ፣ በ1፥3:5-6 ላይ ተገልጦአል:: እግዚአብሔርም ይሁዳ ወደ እርሱ ብትመለስ ወደ እርሷ እንደሚመለስ ተናግሮአል፤ የተናገረውም ቃል ሁልጊዜ ይፈጸማል::

### ትምህርተ መለኮታዊ አስተምህሮው

የመጽሐፉ ትምህርተ መለኮታዊ አስተምህሮ፣ መሲሐዊ እንዲሁም አቡቀለምሲሳዊና ሥነ ፍጻሜያዊ ከሆነ ዐቢይ ሐሳቡ ጋር የተያያዘ ነው:: ዘካርያስ ስለ መሲሑ ሁኔታ በሚገልጽበት ጊዜ፣ ክርስቶስ

ትሑት ሆኖ እንደሚመጣ (6፥12)፣ ሰው መሆኑን (6፥12፤ 13፥7)፣ እንደሚናቅና በሠላሳ ብር እንደ ሚሸጥ (11፥12-13)፣ እንደሚሰቀል (13፥7)፣ ክህነቱን (6፥13)፣ ንጉሥነቱን (6፥13፤ 9፥9፤ 14፥9:16)፣ በክብር እንደሚመጣ (14፥4)፣ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንደሚሠራ (6፥12-13)፣ የአገዛዙ ሁኔታ ምን እንደሚመስል (9፥10፤ 14)፣ ዘላቂ ሰላምንና ብልጽግናን (3፥10፤ 9፥9-10) እንደሚያመጣ አስ ቀድሞ ተናግሮአል:: እነዚህ መሲሑን የሚያመለከቱ ምንባቦች ኢየሱስ በሉቃስ 24፥25-27:44 ላይ ለተ ናገረው ነገር የበለጠ ትርጕም ይሰጡታል::

አቡቀለምሲሳዊና ሥነ ጽሑፋዊ ይዘቱን በሚመለከት ያለውን ሁኔታ ሲገልጽ ኢየሩሳሌም እንደም ትከበብ (12፥1-3፤ 14፥1-2)፣ በመጀመሪያ የይሁዳ ጠላቶች ድል እንደሚያደርጉ (14፥2)፣ እግዚአብሔር ስለ ኢየሩሳሌም እንደሚዋጋ (14፥3-4)፣ በሕዝብ ላይ ፍርድ እንደሚሆን (12፥9፤ 14፥3)፣ የይሁዳ መሬት አቀማመጥ እንደሚለወጥ (14፥4-5)፣ በመሲሑ ዘመነ መንግሥት የዳስ በዓሏ እንደሚከበር (14፥16-19)፣ ኢየሩሳሌምና ሕዝቧ በመጨረሻ እንደሚቀደሱ (14፥20-21) ዘካርያስ ትንቢት ተናግሮአል::

"እግዚአብሔር ያስታውሳል" የሚል ትርጕም ያለው የነቢዩ ስምም ትምህርተ መለኮታዊ ይዘት አለው:: "እግዚአብሔር" የሚለው የአምላክ የግልና የቃል ኪዳን ስሙ ነው፤ ይህም እግዚአብሔር ለሰጠው ተስፋ ታማኝነቱን የሚገልጽ ዘላለማዊ ምስክር ነው (የዘፀ 3፥14 ማብ ይመ):: እግዚአብሔር የኪዳኑን ተስፋ ያስታውሳል፤ ይፈጽመውም ዘንድ ይተጋል:: በዘካርያስ መጽሐፍ ውስጥ እስራኤላውያን የባቢሎን ግዞተኞች ከመሆን ነጻ እንደሚወጡ፣ መንግሥታቸው እንደሚመሠረትና አገልግሎት የሚሰጥ ቤተ መቅደስ እንደሚኖራቸው፣ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ፣ በመሲሑ የሚሆነው ድነትና መታነጽ ምን እንደሚመስል ተብራርቶአል::

በአጠቃላይ መጽሐፉ ቀድሞም ሆነ ዛሬ፣ ወደፊትም እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በሕዝብና በመንግሥታት ላይ ሉዓላዊ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው::

## ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽና መሪ ሐሳብ

ይህ መጽሐፍ ለንስሓ የሚጋብዝ ልመናን (1፥2-6)፣ ትንቢታዊ ራእዮችን (1፥7-6፥8)፣ የፍርድና የድነት ንግሮችን አካቶ የያዘ ነው (ም 9-14):: በ1፥7-6፥8 ላይ የተጠቀሱት ትንቢታዊ ራእዮች አቡቀ ለምሲሳዊ ጽሑፎች ሲሆኑ፣ ለእግዚአብሔር ሕዝብ መጽናናትን የሚሰጡ ጽሑፎች ናቸው:: አቡቀለምሲ ሳዊው ክፍል በም 9-14 ከተጠቀሰው የድነት ቃል ጋር አብሮ ሲነበብ፣ የመጽሐፉ ዋና ሐሳብ በማ ጽናናት ላይ ያተኮረ እንደ ሆነ መረዳት ይቻላል፤ ይህም የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ፊት ታላቅ ክብር የሚጠብቀው በመሆኑ ነው::

በመሠረቱ መጽናናትና ማበረታታት የመጽሐፉ ዐቢይ ሐሳብ ነው፤ የመጀመሪያው ማበረታ ትትም እንደ ገና እየተሠራ ያለውን ቤተ መቅደስ በሚያጠናቅቁበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ ነው:: ይህንም ከግብ ለማድረስና ለማጠናቀቅ የተለያዩ ስልቶች ተግባር ላይ ውለዋል፤ ይህም የመሪ ሐሳቡ አካል ነበር፤ ለምሳሌ የእግዚአብሔር አገዛዝ በመጨረሻ ሙሉ በሙሉ በምድር ላይ ይሰፍን ዘንድ መሲሑ ሲመጣ ታላቅ ጭንቀት እንደሚሆንና መንግሥቱን የሚቃወሙትንም ሁሉ እንደሚያስወግድ በአፅንዖት ይገልጻል::

## አስተዋፅዖ

ክፍል 1 (ም 1-8)

1. መግቢያ (1፥1-6)
   - ሀ. የተጻፈበት ጊዜና የጸሓፊው ስም (1፥1)
   - ለ. የንስሓ ጥሪ (1፥2-6)
2. በሌሊት የታዩ ስምንት ተከታታይ ራእዮች (1፥7-6፥8)
   - ሀ. በፈረስ ተቀምጦ በባርሰነት ዛፎች መካከል የቆመው ሰው (1፥7-17)
   - ለ. አራት ቀንዶችና አራት ጠራቢዎች (1፥18-21)
   - ሐ. የመለኪያ ገመድ የያዘ ሰው (ም 2)
   - መ. ለሊቀ ካህኑ የተሰጠው ንጹህ ልብስ (ም 3)
   - ሠ. የወርቁ መቅረዝና ሁለቱ የወይራ ዛፎች (ም 4)
   - ረ. በራሪው የመጽሐፍ ጥቅልል (5፥1-4)
   - ሰ. በኢፍ መስፈሪያ ውስጥ የተቀመጠችው አንዲት ሴት (5፥5-11)
   - ሸ. አራቱ ሠረገሎች (6፥1-8)
3. በሊቀ ካህኑ በኢያሱ ላይ የተጫነው የመታሰቢያ አክሊል (6፥9-15)
4. ትክክለኛ ያልሆነ ጾም፣ ስለ ወደፊቱ የተሰጠ ተስፋ (ም 7-8)
   - ሀ. ከቤቴል ተወክለው የመጡ ሰዎች ያቀረቡት ጥያቄ (7፥1-3)
   - ለ. የጌታ ተግሣጽ (7፥4-7)
   - ሐ. ንስሓ እንዲገቡ የተሰጠ ትእዛዝ (7፥8-14)
   - መ. ከእግዚአብሔር ሞገስ የተነሣ የእስራኤል ተሐድሶ (8፥1-17)
   - ሠ. በመንግሥቱ ውስጥ የሚሆነው ደስታና የአይሁድ ሞገስ ማግኘት (8፥18-23)

ክፍል 2 (ም 9-14)

5. ሁለት ትንቢታዊ ንግሮች:- የመሲሑ መምጣትና የእግዚአብሔር መንግሥት በሚገባ መታወቅ፣ (ም 9-14)
   ሀ. የመጀመሪያው ንግር:- የመሲሑ መምጣትና ተቀባይነት ማጣት (ም 9-11)
      1. መሲሕ የሆነው ንጉሥ እንደሚመጣ (ም 9-10)
      2. እረኛውና ንጉሡ መሲሕ ተቀባይነት ማጣቱ (ም 11)
   ለ. ሁለተኛው ንግር:- የመሲሑ መምጣትና ተቀባይነት ማግኘት (ም 12-14)
      1. የእስራኤል ነጻ መውጣትና መለወጥ (ም 12-13)
      2. የመሲሑ መምጣትና መንግሥቱ (ም 14)

## ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ የቀረበ ጥሪ

**1** ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት በስ
ምንተኛው ወር የእግዚአብሔር ቃል
ወደ አዶ ልጅ ወደ በራክዩ ልጅ ወደ ነቢዩ
ዘካርያስ እንዲህ ሲል መጣ፤
[2]“እግዚአብሔር በአባቶቻችሁ ላይ እጅግ
ተቈጥቶ ነበር፤ [3]ስለዚህ ለሕዝቡ ንገር፤
እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ ‘ወደ
እኔ ተመለሱ’ ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት፤
‘እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ፤’ ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት፤ [4]የቀደሙት ነቢያት፣
‘እግዚአብሔር ጸባኦት፣ “ከክፉ መንገዳች
ሁና ከክፉ ሥራችሁ ተመለሱ” ይላል፤ በማ
ለት ለአባቶቻችሁ ሰብከው ነበር፤ እነርሱ
ግን አልሰሙም፤ እኔንም አላደመጡም፤ እንደ
እነርሱ አትሁኑ፤ ይላል እግዚአብሔር። [5]አባ
ቶቻችሁ አሁን የት አሉ? ነቢያትስ ለዘላለም
በሕይወት ይኖራሉን? [6]ለባሪያዎቼ ለነቢያት
ያዘዝኋቸው ቃልና ሥርዐት በአባቶቻችሁ
ላይ አልደረሰምን?
“እነርሱም ንስሓ ገብተው፤ እንዲህ አሉ፤
‘እግዚአብሔር ጸባኦት በወሰነው መሠረት፣
ለሥራችንና ለመንገዳችን የሚገባውን አድ
ርጎብናል።’ ”

## በባርሰነት ዛፎች መካከል የቆመው ሰው

[7]ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት፣
ሳባጥ በሚባለው በዐሥራ አንደኛው ወር
በሃያ አራተኛው ቀን፣ የእግዚአብሔር ቃል

1፥1 ቍ7፤ዕዝ 4፥24፤ 5፥1፤6፥15፤ ነህ12፥4፤ማቴ23፥35፤ ሉቃ11፥51
1፥2 2ዜና36፥16
1፥3 ኢዮ22፥23፤ ሚል3፥7፤ያዕ4፥8
1፥4 2ነገ17፥13፤ 2ዜና፤24፥19፤36፥ 15፤መዝ78፥8፤106፥ 6፤ኤር6፥17፤23፤ 23፥22፤ሕዝ20፥18፤ 33፥4፤ዘካ7፥7
1፥6 ዘዳ28፥2፤ ኢሳ44፥26፤ ኤር12፥14-17፤ 23፥20፤39፥16፤ 44፥17፤ሰቆ2፥17፤ ዳን9፥12፤ሆሴ5፥9
1፥7 ቍ1
1፥8 ዘካ6፥2-7፤ ራእ6፥4
1፥9 ዳን7፥16፤ ዘካ4፥14-5፤5፥5
1፥10 ዘካ6፥5-8
1፥11 ዘፍ16፥7፤ ኢሳ14፥7
1፥12 2ዜና36፥21፤ መዝ6፥3፤40፥11፤ ኤር40፥5፤ዳን9፥2
1፥13 ኢዮ15፥11፤ ኢሳ35፥4፤ዘካ4፥1
1፥14 ኢሳ26፥11፤ ኢል2፥18

ወደ አዶ ልጅ ወደ በራክዩ ልጅ ወደ ነቢዩ
ዘካርያስ እንዲህ ሲል መጣ፤
[8]በምሽት ራእይ አየሁ፤ እዚያም በፊቴ
አንድ ሰው በመጋላ ፈረስ ላይ ተቀምጦ
አል፤ እርሱም በሸለቆ ውስጥ በባርሰነት ዛፎች
መካከልም ቆሞ ነበር፤ ከበስተ ኋላውም
መጋላ፣ ሐመርና አንባላይ ፈረሶች ነበሩ።
[9]እኔም፣ “ጌታዬ ሆይ፤ እነዚህ ምንድን
ናቸው?” አልሁ።
ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክም፣
“እነዚህ ምን እንደ ሆኑ አሳይሃለሁ” አለኝ።
[10]ከዚያም በባርሰነት ዛፎች መካከል የቆ
መው ሰው፣ “እነዚህ በምድር ሁሉ እንዲ
መላለሱ እግዚአብሔር የላካቸው ናቸው” ሲል
መለሰ። [11]እነርሱም በባርሰነት ዛፎች መካ
ከል ቆሞ ለነበረው የእግዚአብሔር መልአክ፣
“በምድር ሁሉ ተመላለስን፤ መላዋ ምድ
ርም ዐርፋ በሰላም ተቀምጣለች” ብለው
መለሱለት።
[12]ከዚያም የእግዚአብሔር መልአክ፣ “እግዚ
አብሔር ጸባኦት ሆይ፤ በእነዚህ ሰባ ዓመ
ታት ውስጥ የተቈጣሃቸውን ኢየሩሳሌም
ንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው
እስከ መቼ ነው?” አለ። [13]እግዚአብሔርም
ከእኔ ጋር ይነጋገር ለነበረው መልአክ ደስ
በሚያሰኝና በሚያጽናና ቃል መለሰለት።
[14]ከዚያም ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው
መልአክ እንዲህ አለኝ፤ “ይህን ቃል ተና
ገር፤ እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
‘ስለ ጽዮንና ስለ ኢየሩሳሌም እጅግ ቀንቻ

1፥1፤ *በሁለተኛው ዓመት በስምንተኛው ወር፤* በ520 ዓ.ቅ.ክ ከጥቅምት እስከ ኅዳር ያለውን ጊዜ የሚያመለክት ነው። ሐጌም፣ ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት ፣በስድስተኛው ወር፣ በመጀመሪያው ቀን ማለትም ነሐሴ 29 ቀን 520 ዓ.ቅ.ክ (ሐጌ 1፥1) የነቢይነት አገልግሎቱን ጀመረ። *የእግዚአብሔር ቃል፤* የትንቢትን ቃል መገለጥ የሚያመለክት የተለመደ ሐረግ ነው(9፥1፤12፥1፤ ኤር1፥2፤ ሕዝ1፥3፤ሆሴ1፥1፤ኢዩ1፥1፤ ዮና1፥1፤3፥1፤ሚክ1፥1፤ሶፎ1፥1፤ ሐጌ1፥1፤ሚል1፥1 ይመ፤እንዲሁም የ6፥9ማብ ይመ። *አዶ፤* ቍ7፤ ዕዝ 5፥1፤6፥14፤ነህ12፥4:16 ይመ። እንዲሁም ከመግቢያው “ጸሐፊው” የሚለውን ይመ። *ነቢዩ፤* የእግዚአብሔር አፍ ለመሆን በራሱ በእግዚአብሔር የተጠራ ማለት ነው የዘፀ7፥1-2 ማብ ይመ።

1፥2፤ *በአባቶቻችሁ ላይ እጅግ ተቈጥቶ ነበር፤* ከባቢሎን ምርኮ በፊት የነበሩት የአይሁድ አባቶች፤ ኪዳኑን በማፍረስ እግዚአብሔርን ስለ በደሉ እግዚአብሔር ቀጣቸው፤ ከዚህም የተነሣ በ586 ዓ.ቅ.ክ ላይ ኢየሩሳሌም ተደመሰሰች፤ ሕዝቡም ወደ ባቢሎን ተጋዘ። እግዚአብሔር የሚቀጣ መሆኑን መካድ ሁለንተናዊ ማንነት ያለው አምላክ መሆኑን መካድ ነው።

1፥3፤ *‘ወደ እኔ ተመለሱ’... ‘እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ’፤* ከ7፥13 ጋር ያነጻጽሩ። በዘካርያስ ዘመን የነበሩ ሰዎች አባቶቻቸው የሄዱበትን ክፉ መንገድ በመተው (ቍ4) ወደ እግዚአብሔር ቢመለሱ፣ እግዚአብሔር ወደ እነርሱ ይመለሳል፤ በርግማንም ፈንታ በረከትን ያፈስስላቸዋል ቍ16፤ ኤር18፥710 ይመ።

1፥4፤ *የቀደሙት ነቢያት፤* እንደ ኢሳይያስ (ኢሳ 45፥22 ይመ)፣ እንደ ኤርምያስና (ኤር18፥11 ይመ) ሕዝቅኤል (ሕዝ 33፥11 ይመ) ያሉትን ነው። እንዲሁም 7፥7:12፤ ኤር25፥4-5፤ 35፥15 ይመ።

1፥5፤ *ለዘላለም በሕይወት ይኖራሉን?* አይኖሩም፤ በእነርሱ የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ግን እስኪፈጸም ድረስ ይኖራል (ቍ6 ይመ)።

1፥6፤ *ያዘዝኋቸው ቃልና...በአባቶቻችሁ ላይ አልደረሰምን?* ከኢሳ 40፥6-8፤55፥10-11ጋር ያነጻጽሩ። “አልደረሰምን?” የሚለውን ዘይቤያዊ አገላለጽ በተመለከተ በዘዳ28፥2:15:45 ይመ። *ለባሪያዎቼ ለነቢያት፤* 2ነገ9፥7፤17፥13:23፤21፥10፤24፥2፤ ዕዝ9፥11፤ኤር7፥25 እና ማብ ይመ፤25፥4፤ ሕዝ38፥17፤ዳን 9፥6:10፤ አሞ3፥7ይመ። *ንስሓ ገብተው፤* ከምርኮ በፊት በነበሩት አባቶች ላይ፣ በምርኮ ወቅት ደግሞ በልጆቻቸው ላይና ከምርኮ በኋላም በነበሩት ላይ የደረሰውን ማመልከቱ ግልጽ ነው ከዕዝ 9፤10፥1-17፤ከዳን 9፥1-19ጋር ያነጻጽሩ።

1፥7-17፤ የዘካርያስ የመጀመሪያው ራእይ ነው። የእግዚአብሔር የኪዳን ሕዝብ በመከራ ውስጥ ሳሉ ጠላቶቻቸው ቢመቻቸውም፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚቀና በመሆኑ (የዘፀ 20፥5 ማብ ይመ) ሕዝቡን፣ ከተማቸውንና ቤተመቅደሱን መልሶ ያድሳል። በዚህ በመጀመሪያ ራእይ ውስጥ ያሉት ምሳሌያዊ ገለጻዎች በስምንተኛውና በመጨረሻው ራእይ ውስጥም ተንጸባርቀዋል 6፥1-8።

1፥7፤ *ሳባጥ...በሃያ አራተኛው ቀን፤* የካቲት 15 ቀን 519 ዓ.ቅ.ክ ላይ ነው። ይህም በቍ1 ላይ ከተጠቀሰው ቀን ሦስት ወር በላይ ነው።

1፥8፤ *በምሽት፤* ዘካርያስ ስምንቱንም ራእዮች ያየው በአንዲት ምሽት ነበር 1፥7-6፥8። *ራእይ፤* ሕልም አይደለም 4፥1ይመ። ለዘካርያስ ራእይ የተሰጠው ከእንቅልፉ ሙሉ ለሙሉ ነቅቶ ሳለ ነው። *አንድ ሰው...ላይ ተቀምጦአል፤* የእግዚአብሔር መልአክ ነው ቍ11። በቍ9፥13-14:19፤2፥3፤4፥1:4-5፤5፥5:10፤ 6፥4-5 ላይ ከተጠቀሰውና ራእዩን ከሚተረጕመው መልአክ ይለያል። *ፈረሶች፤* የተላኩ መላእክት ሊሆኑ ይችላሉ ቍ10።

1፥11፤ *የእግዚአብሔር መልአክ፤* የዘፍ16፥7 ማብ ይመ። *ዐርፋ፤* ከ6፥8 ጋር ያነጻጽሩ። የፋርስ መንግሥት በሰላም የሚኖርበት ጊዜ ቢሆንም ቍ15፣ በይሁዳ ያሉት አይሁድ ግን በባዕድ መንግሥት ተጽእኖ ሥር ነበሩ ቍ12።

1፥12፤ *ሰባ ዓመታት፤* 7፥5እና ማብ ይመ። ኤር25፥11-12 እና ማብ ይመ፤ 29፥10 ይመ፤ ከ2ዜና36፥21፤ዕዝ1፥1፤ዳን9፥2 ጋር ያነጻጽሩ።

1፥13፤ *በሚያጽናና ቃል፤* ከቍ14-17 ያሉትን ያመለክታል።

1፥14፤ *ቀንቻለሁ፤* 8፥2 ይመ። እግዚአብሔር ለይሁዳ ያለውን ፍቅር የሚያሳይ ነው። የዘፀ20፥5 ማብ ይመ፤ ከያዕ4፥4 ጋር ያነጻጽሩ። ዋና ሐሳቡም በይሁዳ ላይ የተፈጸመውን ዐመፅ እግዚአብሔር ይበቀላል የሚል ነው (ቍ15)።

ለሁ፤ 15ሰላም አለ በሚሉ አሕዛብ ላይ ግን
በጣም ተቈጥቻለሁ፤ በመጠኑ ተቈጥቼ ሳለሁ፣
እነርሱ ግን ጥፋቱ እንዲብስ አደረጉ።’
16“ስለዚህ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
‘በምሕረት ወደ ኢየሩሳሌም እመለሳለሁ፤
በዚያም ቤቴ እንደ ገና ይሠራል፤ መለኪያ
ገመድም በኢየሩሳሌም ላይ ይዘረጋል’
ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት።
17“ቀጥለህም እንዲህ እያልህ ስበክ፤
*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ ‘ከተ
ሞቼ እንደ ገና ብልጽግና ይትረፈረፍባቸ
ዋል፤*እግዚአብሔርም* እንደ ገና ጽዮንን ያጽ
ናናል፤ ኢየሩሳሌምንም ይመርጣል።’”

## አራቱ ቀንዶችና አራቱ የእጅ ሙያተኞች

18ከዚያም ወደ ላይ ተመለከትሁ፤ ከፊቴም
አራት ቀንዶችን አየሁ፤ 19ከእኔ ጋር
ይነጋገር የነበረውንም መልአክ፣ “እነዚህ
ምንድን ናቸው?” አልሁት።
እርሱም፣ “እነዚህ ይሁዳን፣ እስራኤልንና
ኢየሩሳሌምን የበታተኑ ቀንዶች ናቸው” አለኝ።
20ከዚያም *እግዚአብሔር* አራት የእጅ
ሙያተኞችን አሳየኝ። 21እኔም፣ “እነዚህስ
ምን ሊያደርጉ መጡ?” አልሁ።
እርሱም፣ “እነዚህ ቀንዶች ማንም ራሱን
ቀና ማድረግ እንዳይችል ይሁዳን የበታ
ተኑ ናቸው፤ እነዚህ የእጅ ሙያተኞች ግን
የመጡት እነርሱን ሊያስደነግጧቸው፣ ሕዝ
ቡን ለመበታተን በይሁዳ ምድር ላይ ቀንዳ
ቸውን ያነሡትን የእነዚህን የአሕዛብ ቀን
ዶች ሰብሮ ለመጣል ነው” አለኝ።

## የመለኪያ ገመድ የያዘ ሰው

2 ደግሞም ወደ ላይ ተመለከትሁ፤ እነሆ፤
በእጁ የመለኪያ ገመድ የያዘ ሰውም
በፊቴ አየሁ፤ 2እኔም፣ “የት ልትሄድ ነው?”
አልሁት።
እርሱም፣ “የኢየሩሳሌም ርዝመትና ስፋት
ምን ያህል እንደ ሆነ ለመለካት መሄዴ
ነው” አለኝ።
3ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መል
አክም ሄደ፤ ሌላም መልአክ ሊገናኘው መጣ፤
4እንዲህም አለው፣ “ሩጥና ለዚያ ጕልማሳ
እንዲህ ብለህ ንገረው፤ ‘በውስጧ ካለው የሰ
ውና የከብት ብዛት የተነሣ፣ ኢየሩሳሌም
ቅጥር እንደሌላት ከተማ ትሆናለች፤ 5እኔ
ራሴ በዙሪያዋ የእሳት ቅጥር እሆንላታለሁ፣’
ይላል *እግዚአብሔር* ‘በውስጧም ክብሯ
እሆናለሁ።’
6“ኑ! ኑ! ውጡ ከሰሜን ምድር አም
ልጡ” ይላል *እግዚአብሔር*፤ “ለአራቱ የሰ
ማይ ነፋሳት በትኛችኋለሁና፤” ይላል *እግዚ
አብሔር*።
7“አንቺ ጽዮን ነዪ፤ ከባቢሎን ሴት ልጅ
ጋር የምትኖሪ ሆይ፤ ኰብልዪ።” 8*እግዚአብ
ሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላልና፤ “ካከበረኝና
በዘረፉአችሁ አሕዛብ ላይ ከላከኝ በኋላ፣
የሚነካችሁ የዐይኑን ብሌን ይነካል፤ 9እነሆ፤
እጄን በእነርሱ ላይ አነሣለሁ፤ ባሪያዎቻቸ
ውም ይዘርፏቸዋል፤ ከዚያም *እግዚአብሔር*
ጸባኦት እኔን እንደ ላከኝ ታውቃላችሁ።
10“የጽዮን ልጅ ሆይ፤ እልል በዪ፤ ደስም
ይበልሽ፤ እኔ እመጣለሁና፤ በመካከልሽም
እኖራለሁ” ይላል እግዚአብሔር። 11“በዚያ
ቀን ብዙ አሕዛብ ወደ *እግዚአብሔር* ይጠ
ጋሉ፤ የእኔም ሕዝብ ይሆናሉ። በመካከ
ልሽ እኖራለሁ፤ *እግዚአብሔር* ጸባኦት ወደ
አንቺ እንደላከኝም ታውቃላችሁ። 12*እግዚአ
ብሔርም* በተቀደሰችው ምድር ይሁዳን
ርስቱ አድርጎ ይወርሳል፤ ኢየሩሳሌምንም
እንደ ገና ይመርጣል።

1፥15 2ዜና28፥9፤ መዝ51፥18፤ ኢሳ 14፥1፤ 40፥1፤54፥8-10፤61፥4
1፥16 ዕዝ1፥1፤ ኢዮ38፥5፤ ዘካ2፥1-2፤8፥3
1፥17 ዕዝ9፥9፤ መዝ51፥18፤ኢሳ 14፥1፤40፥1፤54፥8-10፤61፥4
1፥19 አሞ6፥13
1፥21 1ነገ22፥11፤ መዝ75፥4፡10፤ኢሳ 54፥16-17፤ ዘካ12፥9
2፥2 ሕዝ40፥3፤ ዘካ1፥16፤ራእ21፥15
2፥4 ኢሳ49፥20፤ ኤር30፥19፤33፥22፤ ሕዝ38፥11፤ዘካ14፥11
2፥5 መዝ46፥5፤ 85፥9፤125፥2፤ ኢሳ10፥17፤11፥10፤ 24፥23፤26፥1፤ ሕዝ 38፥14፤ 42፥20፤ ራእ21፥23
2፥6 መዝ44፥11፤ ሕዝ17፥21፤37፥9፤ ማቴ24፥31፤ማር 13፥27
2፥7 ኢሳ42፥7፤ 48፥20፤ኤር3፥18
2፥8 ዘዳ32፥10
2፥9 ኢሳ14፥2፤ 48፥16፤ኤር12፥14፤ ዕን2፥8፤ዘካ4፥9፤ 6፥15
2፥10 ዘፀ25፥8፤ ዘሌ26፥12፤ዘኍ 23፥21፤ኢሳ23፥12፤ ሶፎ3፥14፤ዘካ8፥3፤ 9፥9፤ራእ21፥3
2፥11 ኤር24፥7፤ ሚክ4፥2፤ዘካ4፥9፤6፥ 15፤8፥8:20-22
2፥12 ዘፀ34፥9፤ ዘዳ12፥5፤መዝ 33፥12፤ኢሳ14፥1፤ ኤር10፥16፤40፥5

1፥15፤ *ጥፋቱ እንዲብስ አደረጉ፤* እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ስለተቈጣ፣ አሦራውያንንና (ኢሳ10፥5) ባቢሎናውያንን (ኢሳ47፥6፤ኤር25፥9) ተጠቅሞ ቢቀጣቸውም፣ አሦራውያንና ባቢሎናውያን ግን ከዚህ አልፎ በመሄድ የአይሁድን ሕዝብ ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ሞከሩ።

1፥16፤ *በምሕረት፤* ወይም፣ “እናት ለልጅዋ ያላት ርኅራኄ” ዐይነት ነው ቍ12 ይመ። *እመለሳለሁ፤* የቍ3 ማብ ይመ። *ቤቴ እንደገና ይሠራል፤* ዕዝ6፥14-16 ይመ። *መለኪያ ገመድም፣* የተሐድሶ ምልክት ነው ከኤር31፥38-40 ጋር ያነጻጽሩ።

1፥17፤ *ኢየሩሳሌምንም ይመርጣል፤* 2፥12፤3፥2 ይመ።

1፥18-21፤ የዘካርያስ ሁለተኛው ራእይ ነው፤ እስራኤልን ባድማ ያደረጉ መንግሥታት (ቍ19) እነርሱም እንደዚሁ በሌሎች መንግሥታት ፈጽመው ይጠፋሉ።

1፥18፤ *አራት፤* ቍጥሩ ቃል በቃል የሚወሰድ ከሆነ አሦርን፣ ግብፅን፣ ባቢሎንንና ሜዶንና ፋርስን የሚያመለክት ነው። *ቀንዶችን፤* በጥቅሉ የጥንካሬ ምልክት (መዝ18፥2) ወይም የአንድን አገር ብርታት ማለትም ንጉሥዋን (መዝ 89፥17፤ ዳን 7፥78፤ 8፥20-21፤ራእ17፥12) ወይም ቍ21 በዚህ ቦታ እንደተገለጸው በአጠቃላይ የአንድን ሕዝብ ኀይል የሚያመለክት ነው።

1፥20፤ *አራት የእጅ ሙያተኞችን፤* ቍጥሩ ቃል በቃል የሚወሰድ ከሆነ ግብፅን፣ ባቢሎን፣ፋርስንና ግሪክን የሚያመለክት ነው፤ ይህ የይሁዳ ጠላቶች በሙሉ በመጨረሻ እንደሚሸነፉ ግልጽ የሚያደርግ ነው (ቍ21)።

2፥1-13፤ የዘካርያስ ሦስተኛ ራእይ ነው። የቃል ኪዳኑ ሕዝብ፣ ቤተ መቅደሱና ከተማዋ ሙሉ በሙሉ እንደሚታደሱና እንደ ሚባረኩ የሚያመለክት ነው።

2፥1፤ *የመለኪያ ገመድ፤* የ1፥16 ማብ ይመ።

2፥4፤ *ጕልማሳ፤* ዘካርያስ መሆኑ ግልጽ ነው። *ቅጥር እን ደሌላት፤* በቅጥር እስከማይወሰኑ ድረስ የከተማዋ ሕዝብ እጅግ ይበዛል 10፥8፡10፤ኢሳ49፥19-20 ማብ ይመ።

2፥5፤ *የእሳት ቅጥር፤* ለመለኮታዊው ጥበቃ ትእምርት ነው ዘፀ13፥21እና ማብ ይመ፤ኢሳ4፥56 እና ማብ ይመ። *ክብሯ፤* ዘፀ 40፥34 ይመ።

2፥6፤ *ከሰሜን ምድር፤* ባቢሎን (ቍ7) ከሰሜን መጥታ ነው ይሁዳን የወረረችው (ኤር1፥14፤4፥6፤6፥1፡22፤10፥22)። *ለአራቱ የሰማይ ነፋሳት፤* በሁሉም አቅጣጫ ማለት ነው። በምርኮ ያለው ሕዝብ ከሰሜን፣ ከደቡብ፣ ከምሥራቅና ከምዕራብ ተመ ልሶ ይመጣል ኢሳ43፥56፤49፥12።

2፥7፤ *ጽዮን፤* በባቢሎን ያሉ ከኢየሩሳሌም የተወሰዱ ምርኮኞችን ያመለክታል። *ከባቢሎን...ኰብልዪ፤* ከራእ18፥48 ጋር ያነጻጽሩ።

2፥8፤ *የዐይኑን ብሌን፤* የዘዳ32፥10 ማብ ይመ።

2፥9፤ *እጄን፤* የኀይል ምሳሌ ነው።

2፥10፤ 9፥9 ይመ። *በመካከልሽም እኖራለሁ፤* ቍ11፤8፥3፤ ዘሌ26፥11-12፤ሕዝ37፥27፤ ዮሐ1፥14፤2ቆሮ6፥16፤ራእ21፥3 ይመ።

2፥11፤ *ብዙ አሕዛብ፤* ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ ይፈ ጸም ዘንድ (ዘፍ12፥3ይመ፤ዘካ8፥20-23፤ዘፍ18፥18፤22፥18፤ኢሳ2፥2-4፤60፥3ጋር ያነጻጽሩ)። *በዚያ ቀን፤* የጌታን ቀን ያመለክታል (3፥10 እንዲሁም የኢሳ2፥11፡17፡20ማብ ይመ)።

2፥12፤ *በተቀደሰችው ምድር፤* በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምድሪቱ በዚህ መልኩ የተጠራችው በዚህ ስፍራ ብቻ ነው፤ ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት የቅዱሱ ንጉሥ የእግዚአብሔር ቤተ

13 *እግዚአብሔር* ከተቀደሰ ማደሪያው ተነሥ
ቶአልና፣ ሥጋ ለባሽ ሁሉ ሆይ፤ በፊቱ ጸጥ በል።

## ለሊቀ ካህኑ የሚሆን ንጹሕ ልብስ

**3** እርሱም ሊቀ ካህኑን ኢያሱን[^] *በእግዚአ*
*ብሔር* መልአክ ፊት ቆሞ፣ ሰይጣንም[ሐ]
ሊከሰው በስተ ቀኙ ቆሞ አሳየኝ። 2*እግዚ*
*አብሔርም* ሰይጣንን፣ "አንተ ሰይጣን፤ *እግ*
*ዚአብሔር* ይገሥጽህ፤ ኢየሩሳሌምን የመረጠ
*እግዚአብሔር* ይገሥጽህ፤ ይህ ሰው ከእሳት
የተነጠቀ ትንታግ አይደለምን?" አለው።
3ኢያሱም ያደፈ ልብስ ለብሶ በመልአኩ
ፊት ቆሞ ነበር። 4መልአኩም ከፊቱ ቆመው
የነበሩትን፣ "ያደፉ ልብሶቹን አውልቁለት"
አላቸው።
ኢያሱንም፣ "እነሆ፤ ኀጢአትህን ከአንተ
አስወግጃለሁ፤ ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ"
አለው።
5እኔም፣ "ንጹሕ ጥምጥም በራሱ ላይ አድር
ጉለት" አልሁ። *የእግዚአብሔርም* መልአክ
በአጠገቡ ቆሞ እያለ፣ ንጹሕ ጥምጥም በራሱ
ላይ አደረጉለት፤ ልብስም አለበሱት።
6*የእግዚአብሔርም* መልአክ ለኢያሱ ይህን
ማስጠንቀቂያ ሰጠው፤ 7"*እግዚአብሔር* ጸባ
ኦት እንዲህ ይላል፤ 'በመንገዴ ብትሄድ፣
ትእዛዜንም ብትጠብቅ፣ ቤቴን ታስተዳድራ
ለህ፤ በአደባባዮቼም ላይ ኀላፊ ትሆናለህ፤
በዚህ በቆሙት መካከል ቦታ እሰጥሃለሁ።
8" 'ሊቀ ካህኑ ኢያሱ ሆይ፤ ስማ፤ በፊትህ
የሚቀመጡትም ረዳቶችህ ገና ወደ ፊት
ለሚመጡት ምልክት የሚሆኑ ሰዎች ናቸ
ውና ይስሙ፤ እነሆ፤ ባሪያዬን ቍጥቋጡን
አመጣለሁ። 9በኢያሱ ፊት ያስቀመጥሁት
ድንጋይ እነሆ! በዚያ በአንዱ ድንጋይ ላይ
ሰባት ዐይኖች[ሐ] አሉ፤ በእርሱም ላይ ቅርጽ
እቀርጻለሁ፤ የዚህችንም ምድር በደል በአ
ንድ ቀን አስወግዳለሁ፤' ይላል *እግዚአብሔር*
ጸባኦት።
10" 'በዚያን ቀን እያንዳንዱ በገዛ ወይኑና
በለሱ ሥር ሆኖ ባልንጀራውን ይጋብዛል፤'
ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት።"

2፥13 ዘፀ14፥14፤ ዘዳ26፥15፤ ኢሳ41፥1
3፥1 2ሳሙ24፥1፤ 2ዜና18፥21፤ ዕዝ2፥2፤ መዝ109፥6፤ ዘካ6፥11፤ ማቴ4፥10
3፥2 ኢሳ7፥4፤ 14፥1፤ ይሁ1፥9:23
3፥4 ዘፍ41፥42፤ 2ሳሙ12፥13፤ መዝ132፥9፤ ኢሳ52፥1፤ ሕዝ 36፥25፤ ሚክ7፥18፤ ራእ19፥8
3፥5 ዘፀ29፥6
3፥7 ዘሌ8፥35፤ ዘዳ17፥8-11፤ 2ዜና23፥6፤ ኤር15፥1 9፤ ሕዝ44፥15-16፤ ዘካ6፥15
3፥8 ዘዳ28፥46፤ ኢሳ4፥2፤ 49፥3፤ ሕዝ12፥11፤ 17፥22፤ ሐጌ1፥1
3፥9 2ሳሙ12፥13፤ 2ዜና16፥9፤ ዕዝ2፥2፤ ኢሳ28፥16፤ ኤር50፥20
3፥10 ዘኍ 16፥14፤ 1ነገ4፥25፤ ኢዮ11፥18፤ ሚክ4፥4
4፥1 ኤር31፥26፤ ዳን8፥18
4፥2 ዘፀ25፥31፤ ኤር1፥13፤ ራእ 1፥12፤ 4፥5

## የወርቁ መቅረዝና ሁለቱ የወይራ ዛፎች

**4** ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክም
ተመልሶ፣ አንድ ሰው ከእንቅልፉ እንደ
ሚነቃ አነቃኝ፤ 2እርሱም፣ "ምን ታያለህ?" አለኝ።
እኔም እንዲህ አልሁ፤ "እነሆ፤ በዐናቱ
ላይ የዘይት ማሰሮ ያለበት ሁለንተናው
ወርቅ የሆነ መቅረዝ አየሁ፤ በመቅረዙም
ላይ ሰባት ቧንቧዎች ያሏቸው ሰባት መብ

[^]1 *የየሽዋ* ለሚለው ተለዋጭ ስም ነው፤ እዚህ ላይ እንዲሁም በዘካርያስ መጽሐፍ በሌሎች ቦታ።
[ሐ]1 *ሰይጣንም* ትርጉሙ ከሳሽ ማለት ነው።

*መቅደስና ዙፋኑ በምድር የተቀመጠበት፣* እርሱም ከኪዳኑ ሕዝብ ጋር አብሮ የሚኖርበት ቦታ በመሆኑ ነው። የዘፀ3፥5 ማብ ይመ። *ኢየሩሳሌምንም..ይመርጣል፤* 1፥17፤3፥2 ይመ።

2፥13፤ *በፊቱ ጸጥ በል፤* ዕን 2፥20፤ ሶፎ1፥7ይመ። *ተነሥቶአልና፤* ሊፈርድ ማለት ነው ከቍ9 ጋር ያነጻጽሩ።

3፥1-10፤ የዘካርያስ አራተኛው ራእይ ነው፤ እስራኤል የካህናት ሕዝብ እንድትሆን ከኀጢአቷ ትነጻለች፤ እንደገናም ትታደሳለች (ዘፀ19፥6 እና ማብ ይመ)።

3፥1፤ *ኢያሱን፤* ይህ ሰው በዚህ ክፍል ኀጢአተኛ የሆነውን የእስራኤልን ሕዝብ ወክሎአል (ቍ8-9 ይመ)። በጥንት ጊዜ ይህ ስም የተለመደ ነበር፤ ግሪኩ ወደ አማርኛ ሲመለስ "ኢየሱስ" ማለት ሲሆን፣ "እግዚአብሔር ያድናል" ማለት ነው (የማቴ1፥21 ማብ ይመ)። *በእግዚአብሔር መልአክ፤* 1፥11ይመ፤ እንዲሁም የዘፍ16፥7 ማብ ይመ። *በ...ፊት ቆሞ፤* እንደ ካህን ሆኖ በፊቱ ማገልገሉን ያመለክታል (ዘዳ10፥8፤2ዜና29፥11፤ሕዝ44፥15 ይመ)። *ሰይጣንም፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ። ከኢዮ1፥6፤2፥1-7፤ራእ 12፥10 ጋር ያነጻጽሩ። *ሊከሰው፤* በዕብራይስጡ ይህ ቃልና ሰይጣን የሚለው ስም የተገኙት ከአንድ ቃል ነው። *በስተቀኙ፤* መዝ109፥6 ይመ።

3፥2፤ *ይገሥጽህ ይገሥጽህ፤* የተደገመው ለአጽንዖት ነው (4፥7 ይመ፤ እንዲሁም የኢሳ 40፥1 ማብ ይመ)። *ኢየሩሳሌምን የመረጠ፤* 1፥17፤2፥12 ይመ። *ከእሳት የተነጠቀ ትንታግ፤* አይሁድ ከባቢሎናውያን የምርኮ እሳት የዳኑት እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን የወደፊት ዐላማና ዕቅድ እንዲፈጽሙ ነው፤ (አሞ4፥11፤ ዘካ13፥8-9፤ ዘዳ4፥20እና ማብ ይመ፤7፥7-8፤1ነገ8፥51፤ኢሳ48፥10፤ኤር 11፥4፤ 30፥7፤ራእ12፥13-16 ይመ)።

3፥4፤ *ከፊቱ ቆመው የነበሩትን፤* መላእክት ሳይሆኑ አይቀርም (እንዲሁም ቍ7ይመ)። *ያደፉ ልብሶቹን አውልቁለት፤* ለክህነት አገልግሎቱ የማያበቁትን ነው፤ ይህም ከኀጢአት የመንጻት ትእምርት ነው (የቍ9 ማብ ይመ)።

3፥5፤ *ንጹሕ ጥምጥም በራሱ ላይ አድርጉለት፤* ታላቅ ወደ ሆነ የክህነት አገልግሎት የተመለሰ በእግዚአብሔር ፊት ስለ እስራኤል እንዲቆም የተሾመ ካህን እስራኤል ማግኘቷን ያመለክታል። በጥምጥሙ ፊት፣ "ቅድስና ለእግዚአብሔር" የሚል ጽሑፍ ነበረበት (ዘፀ28፥36፤ 39፥30 ይመ፤ ከ14፥20ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥7፤ ኢያሱና ከእርሱ ጋር ያሉት ካህናት ታማኝ ከሆኑ እግዚአብሔር ለጽዮንና ለእስራኤል ያለውን ዐላማና ዕቅድ ከሚፈጽሙት መላእክት ጋር አብረው ይሠሩ ነበር። *በዚህ በቆሙት መካከል፤* የቍ4ማብ ይመ።

3፥8፤ *ረዳቶችህ፤* ከእርሱ ጋር የሚያገለግሉ ካህናት ናቸው። *ባሪያዬን፤* የዘፀ14፥31፤መዝ18ርእስ፤ኢሳ41፥8-9፤42፥1-4፤42፥1፤ ሮሜ 1፥1ማብ ይመ። *ቍጥቋጡን፤* ለመሲሑ የተሰጠ ስያሜ ነው (6፥12 ይመ፤ ኢሳ4፥2 እና ማብ ይመ፤11፥1፤ ኤር 23፥5፤ 33፥15 ይመ)።

3፥9፤ *ድንጋይ፤* ምናልባት ለመሲሑ የተሰጠ ሌላ ስያሜ ሊሆን ይችላል (ከመዝ118፥22-23፤ከኢሳ8፥13-15፤28፥16እና ማብ ይመ፤ ዳን2፥35:45፤ከማቴ21፥42፤ኤፌ2፥19-22፤ከ1ጴጥ2፥6-8ጋር ያነጻጽሩ)። *ሰባት ዐይኖች፤* መጨረሻ የሌለውን ዕውቀት፣ "ሁሉን ዐዋቂነት" የሚያመለክት ሊሆን ይችላል (የ4፥10ማብ ይመ)። *የዚህችንም ምድር በደል...አስወግዳለሁ፤* በቍ4 ላይ የተጠቀሰው ትእምርት እዚህ ላይ ተብራርቶአል። "ምድር" የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። በዚህ ስፍራ ስለተነገረው 12፥10-13፡1 ይመ። *በአንድ ቀን፤* ጌታ የተሰቀለበትን ዓርብ ቀን የሚያመለክት ነው፤ አንዳንዶች ግን የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ጭምር ያመለክታል ይላሉ።

3፥10፤ *በዚያን ቀን፤* የጌታን ቀን ማለት ነው (2፥11ይመ እንዲሁም የኢሳ 2፥11፡17፡20 ማብ ይመ)። *በገዛ ወይኑና በለሱ ሥር ሆኖ፤* ሰላምን፣ ዋስትናንና እርካታን የሚያመለክት ሥዕላዊ ገለጻ ነው (2ነገ18፥31፤ሚክ4፥4 እና ማብ ይመ)።

4፥1-14፤ የዘካርያስ አምስተኛው ራእይ ነው። አይሁድ የአምላካቸውን መልካምነት ተመልክተው ቤተ መቅደሱን መልሰው እንዲሠሩ የሚያበረታታ ነው። በቤተመቅደሱ ውስጥ ካለው መቅረዝ የሚወጣው ብርሃን የሚወክለው፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብና በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በሚሰጠው ቅዱስ አገልግሎት የሚገለጸውን የእግዚአብሔርን የክብር መንጸባረቅ ነው (ቍ6፡12፤ የዘፀ25፥31 ማብ ይመ። ይህ ኀይል ዘሩባቤል መቅደሱን መልሶ መሥራት የሚችልበትን ጕልበት ይሰጠዋል (ቍ6-10)። ዘሩባቤል ንጉሣዊውን፣ ኢያሱ ደግሞ የክህነት አገልግሎትን በመወከል ሲያገለግሉ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ለሕዝቡ መቅደሱን መልሰው መሥራት የሚችሉብትን ችሎታ ይሰጣቸዋል (ቍ11-14)።

4፥1፤ *አነቃኝ፤* በዚያው ሌሊት ነው (የ1፥8ማብ ይመ)።

4፥2፤ *ምን ታያለህ?* 5፥2ይመ፤ እንዲሁም ኤር1፥12 እና ማብ ይመ። ምናልባት ይህ ራእይ እንደ ዘይት መያዣ ሆኖ በሚያገለግለው በትልቁ ማሰሮ ዙሪያ ስለ ተደረደሩት ሰባት መብራቶች ነው። "ሰባቱ የመብራት ቧንቧዎች" ዘይቱን ከማሰሮው ወደ መብራቶቹ ይወስዳሉ። ይህ ክፍል ሌላም ትርጕም ሊኖረው ይችላል፤ ይኸውም ቧንቧዎቹ የመብራቱን ክር የሚያስገቡ

ራቶች ነበሩ። 3ደግሞም አንዱ ከዘይቱ ማሰሮ
በስተ ቀኝ፣ ሌላውም በስተ ግራ የሆኑ
ሁለት የወይራ ዛፎች አሉ።"
4ያነጋገረኝ የነበረውንም መልአክ፣ "ጌታዬ
ሆይ፤ እነዚህ ምንድን ናቸው" አልሁት።
5እርሱም፣ "ምን እንደ ሆኑ አታውቅምን?"
አለኝ።
እኔም፣ "ጌታዬ ሆይ፤ አላውቅም" አልሁት።
6ከዚያም እንዲህ አለኝ፤ "ለዘሩባቤል የተ
ላከው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው፤
'በመንፈሴ እንጂ በኀይልና በብርታት አይ
ደለም' ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት።
7"ታላቅ ተራራ ሆይ፤ አንተ ምንድን
ነህ?[ሠ] በዘሩባቤል ፊት ደልዳላ ሜዳ ትሆና
ለህ፤ ሰዎች፣ 'ሞገስ ይሁንለት! ሞገስ ይሁ
ንለት!' ብለው እየጮኹ፣ እርሱ መደምደ
ሚያውን ድንጋይ ያወጣል።"
8ደግሞም የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ
እንዲህ ሲል መጣ፤ 9"የዘሩባቤል እጆች የዚ
ህን ቤተ መቅደስ መሠረት ጣሉ፤ የሚፈ
ጽሙትም የእርሱ እጆች ናቸው። ከዚያም
እግዚአብሔር ጸባኦት እኔን ወደ እናንተ
እንደ ላከኝ ታውቃላችሁ።
10"የጥቂቱን ነገር ቀን የናቀ ማን ነው?
ሰዎች በዘሩባቤል እጅ ቱንቢውን ሲያዩ ይደ
ሰታሉ።
"እነዚህ ሰባቱ በምድር ሁሉ የሚዘዋ
ወሩ የእግዚአብሔር ዐይኖች ናቸው።"
11ከዚያም መልአኩን፣ "ከመቅረዙ በስተ
ቀኝና በስተ ግራ ያሉት እነዚህ ሁለት የወ
ይራ ዛፎች ምንድን ናቸው?" አልሁት።
12እንደ ገናም፣ "በሁለቱ የወርቅ ቧንቧ
ዎች አጠገብ የወርቅ ዘይት የሚያፈሱት
እነዚህ ሁለት የወይራ ቅርንጫፎች ምንድን
ናቸው?" አልሁት።
13እርሱም፣ "ምን እንደ ሆኑ አታውቅ
ምን?" አለኝ።
እኔም፣ "ጌታዬ ሆይ፤ አላውቅም" አልሁት።
14እርሱም፣ "እነዚህ ሁለቱ የምድርን ሁሉ
ጌታ ለማገልገል የተቀቡ[ረ] ናቸው" አለኝ።

### በራሪው የመጽሐፍ ጥቅልል

5 እንደ ገናም ተመለከትሁ፤ በዚያም በፊቴ
በራሪ የመጽሐፍ ጥቅልል አየሁ።
2እርሱም፣ "ምን ታያለህ?" ሲል ጠየ
ቀኝ። እኔም፣ "ርዝመቱ ሃያ ክንድ፣ ወርዱ[ሰ]
ዐሥር ክንድ የሆነ በራሪ የመጽሐፍ ጥቅ
ልል አያለሁ" አልሁት። 3እርሱም እንዲህ
አለኝ፤ "ይህ በምድር ሁሉ ላይ የሚወጣ
ርግማን ነው፤ በአንደኛው በኩል እንደ ተጻ

4፥3 ቍ11፤ መዝ1፥3፤ራ11፥4
4፥5 ዘካ1፥9
4፥6 1ሳሙ2፥9፤ 13፥22፤1ነገ19፥2፤ 1ዜና3፥19፤ዕዝ5፥2፤ ነህ9፥20፤ኢሳ11፥2-4፤ ዳን2፥34፤ሆሴ1፥7
4፥7 1ዜና15፥28፤ መዝ26፥12፤ 118፥22፤ኤር51፥25
4፥9 ዕዝ3፥8፡11፤ 6፥15፤ዘካ2፥9፤6፥12
4፥10 2ዜና16፥9፤ ዕዝ5፥1፤ ነህ12፥1፤ ኢዮ38፥5፤ሐጌ2፥3፡ 23፤ራእ5፥6
4፥11 ቍ3፤ ራእ11፥4
4፥14 ዘፀ29፥7፤ 40፥15፤መዝ45፥7፤ ኢሳ20፥3፤ ዳን9፥24-26
5፥1 መዝ40፥7፤ ኤር36፥4፤ራእ5፥1
5፥2 ኤር1፥13
5፥3 ዘፀ20፥7፡15፤ ኢሳ24፥6፤ 34፥2፤43፥28፤ 48፥1፤ሚል3፥8፡ 9፤4፥6

ሠ9 ወይም ገጾች እንደማለት ነው
ሠ7 ወይም ማለት ነህ ማለት ይሆናል።
ረ14 ወይም እና ሁለቱ ዘይት የሚያመጡ
ሰ2 ዕብራይስጡ፣ርዝመቱሃያ ክንድ፣ ወርዱ 10 ክንድ ወይም ርዝማኔው ዘጠኝ ሜትር፣ ስፋቱ አራት ተኩል ሜትር ይሆናል

የመብራቱ አፎች ሲሆኑ፣ እያንዳንዱም መብራት ሰባት ማስገቢያዎች አሉት፤ ስለዚህ በአጠቃላይ አርባ ዘጠኝ መብራቶች ይኖሩታል ማለት ነው። ማሰሮው የዘይቱን አቅርቦት ያሳያል፤ ይህም እግዚአብሔር በመንፈሱ አማካይነት የሚሰጠው የኀይሉ ሙላት ትእምርት ነው። ሰባት ቍጥር ፍጹምነትንና ሙላትን የሚያመለክት ስለሆነ እንደ ልብ የሚበራውን የመብራቱን ብርሃን ይወክላል።

4፥3፤ *ሁለት የወይራ ዛፎች፤* ከራእ11፥4ጋር ያነጻጽሩ። ሁለቱ የወይራ ዛፎች የንጉሥነትና የክህነትን አገልግሎት ይወክላሉ፤ የማያቋርጠውንም የዘይት አቅርቦት ያመለክታሉ። ሁለቱ የወይራ ቅርንጫፎች (ቍ12) ካህኑ ኢያሱንና (ም 3) ከዳዊት ንጉሣዊ ቤተሰብ የሆነውን ዘሩባቤልን (ም 4፤ ከቍ14ጋር ያነጻጽሩ)ያመለክታሉ። እነዚህ ሁለት መሪዎች በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የእግዚአብሔርን ሥራ የሚሠሩ ናቸው (ቍ6)። ይህም ሥራ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ማገልገልንና የሕዝቡን ሕይወት ማነጽን ያጠቃልላል። የክህነትና የንጉሣዊ አገልግሎት መጣመር የሚመጣውን የመሲሑን የክህነትና የንጉሥነት አገልግሎት የሚያመለክት ነው (ከ6፥13 ጋር ያነጻጽሩ)።

4፥4፤ *እነዚህ፤* በቍ3፡11 ላይ ያሉት ሁለቱ የወይራ ቅርንጫፎች ራእዩን ግልጽ ያደርጋሉ። ለጥያቄው መልስ የተሰጠው ቍ14 ላይ ነው።

4፥6፤ *በኀይልና በብርታት አይደለም፤* ዘሩባቤል ዳዊትና ሰሎሞን የነበራቸውን ያህል ንጉሣዊ ኀይልና ብርታት ባይኖረውም እንኳ ማለት ነው። *በመንፈሴ፤* በቍ12ላይ ያለው የዘይቱ ምሳሌ ትእምርት ፍቺ ነው። መልአኩ፣ ዘሩባቤል የጀመረውን የቤተመቅደሱን ግንባታ እንዲጨርስ በማበረታታት (ቍ7-10) መንፈስ ቅዱስ ኀይል እንደሚሰጠው አረጋገጠለት።

4፥7፤ *ተራራ...ደልዳላ፤* በእግዚአብሔር መንፈስ የሆነ እምነት፣ ተራራ የሚያህለውን ዕንቅፋት ያሸንፋል። በዘይቤያዊ አገላለጽ ይህ ተራራ፣ ተቃውሞንና (ዕዝ4፥1-5፡24) የቤተ መቅደሱን ግንባታ ለማጠናቀቅ የሕዝቡን ፈቃደኛ አለመሆን (ሐጌ 1፥14፤ 2፥15) ሊያመለክት ይችላል፤ ከኢሳ40፥4፤41፥15፤49፥11፤ማቴ 17፥20፤ 21፥21፤ ማር11፥23፤ ከ1ቆሮ13፥2፤2ቆሮ10፥4 ተመሳሳይ አገላለጽ ጋር ያነጻጽሩ። *መደምደሚያውን ድንጋይ፤* ዘሩባቤል ቤተ መቅደሱን አድሶ መጨረሱን (ቍ9ይመ) የሚያመለክት መጨረሻ ላይ የሚደረግ ድንጋይ ነው (መዝ 118፥22)። *ሞገስ ይሁንለት፤ ሞገስ ይሁንለት!* ድግግሞሹ ለአጽንዖት ነው (3፥2 እንዲሁም የኢሳ 40፥1 ማብ ይመ)።

4፥8፤ የ6፥9 ማብ ይመ።

4፥9፤ *መሠረት ጣሉ፤* በ537-536 ዓ.ቅ.ክ ዕዝ3፥8-11፤5፥16 ይመ። *የሚፈጽሙትም፤* በ516 ዓ ቅ ክ ነው ዕዝ6፥14-16 ይመ።

4፥10፤ *የጥቂቱን ነገር ቀን፤* አንዳንዶች የቤተ መቅደሱን ግንባታ ፋይዳ እንደሌለው ነገር ቈጥረውት ነበር (ዕዝ3፥12፤ሐጌ 2፥3)፤ እግዚአብሔር ግን በግንባታው ሥራ ውስጥ ስለ ነበር፣ ዘሩባቤል ሥራውን እንዲጨርስ የእግዚአብሔር መንፈስ ያግዘው ነበር (ቍ6)። *ቱንቢውን፤* የዕብራይስጡ ቃል ትርጕም በትክክል አይታወቅም፤ ነገር ግን፣ "ቱንቢ" የሚለው ቃል ትክክል ከሆነ፣ የቤተ መቅደሱ ሥራ በዘሩባቤል እጅ በተጠናቀቀ ጊዜ፣ ሕዝቡ እንደሚደሰት የሚገልጽ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ቃሉ በዕብራይስጥ የተለየ ወይም የተመረጠ ድንጋይ ማለትም ነው፤ ይህም በቍጥር 7 ላይ የተጠቀሰውን የመደምደሚያ ድንጋይ ያመለክታል። *ሰባቱ... ዐይኖች፤* የ3፥9 ማብ ይመ። እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ ይመለከታል፤ ስለዚህ በይሁዳ ያለው ሁኔታ በቍጥጥሩ ሥር ነው።

4፥14፤ በዚህ ክፍል የራእዩ ትርጕም ተብራርቶአል። *ሁለቱ... የተቀቡ፤* ከዳዊት ንጉሣዊ ወገን የሆነውን ዘሩባቤልንና ከካህናት ወገን የሆነውን ኢያሱን የሚያመለክት ነው። ለቅባት የተጠቀሙበት (ቍ12) መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ነው (ቍ6)። የገዥነትና የክህነት በአንድነት መጣመር የሚያመለክተው የመሲሑን ንጉሣዊ ክህነት ነው (ከ6፥13፤መዝ110፤ዕብ7 ጋር ያነጻጽሩ።) *የምድርን ሁሉ ጌታ፤* ዘሩባቤልና ሕዝቡ የነበሩበትን ሁኔታ መቈጣጠር የሚችለውን ማለት ነው።

5፥1-4፤ የዘካርያስ ስድስተኛው ራእይ ነው፤ ሕግ የጣሱ በዚያው በጣሱት ሕግ ይኰነናሉ። ኀጢአተኞችም ከምድሪቱ ይወገዳሉ።

5፥1፤ *በራሪ፤* ሁሉም ሰው እንዲያነበው ሲባል ያልተጠቀለለ እንደ ሰንደቅ ዐላማ የሚውለበለብ ነው። *የመጽሐፍ ጥቅልል፤* የዘፀ17፥14ማብ ይመ።

5፥2፤ *ምን ታያለህ?* 4፥2ይመ፤ እንዲሁም ኤር1፥11 እና ማብ ይመ። *ሃያ...ዐሥር፤* ከመጠን በላይ ሰፊ የሆነበት ምክንያት፣ ሰው ሁሉ እንዲመለከተው ነው። ኀጢአት ስለሚያስከትለው ፍርድ የሚናገረው ይህ ጕልህ መልእክት፣ ንስሓ የመግባትንና በጽድቅ የመኖርን አስፈላጊነት ያመለክታል።

5፥3፤ *ርግማን፤* ዘዳ27፥26 እና ማብ ይመ። *በአንደኛው... በሌላው፤* ሁለት ገጽታ እንደ ነበረው የሕጉ ጽላት (ዘፀ32፥15) በዚህ

ፈው የሚሰርቅ ሁሉ ይጠፋል፤ በሌላው በኩል
ደግሞ እንደ ተጻፈው በሐሰት የሚምል
ሁሉ ይጠፋልና:: 4*እግዚአብሔር ጸባኦት*
'እኔ ርግማኑን አመጣዋለሁ፤ እርሱም ወደ
ሌባው ቤትና በስሜ በሐሰት ወደሚምለው
ሰው ቤት ይገባል፤ በዚያም ይቀመጣል፤
ቤቱን፣ እንጨቱንና ድንጋዩን ያጠፋል ይላል::"

## በቅርጫት ውስጥ ያለች ሴት

5ከዚያም ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መል
አክ ወደ እኔ መጥቶ፣ "ወደ ላይ ተመልከት፤
ይህ የሚመጣው ምን እንደ ሆነ እይ" አለኝ::
6እኔም፣ "ምንድን ነው?" አልሁት::
እርሱም፣ "የኢፍ መስፈሪያ[a] ነው" አለኝ::
ቀጥሎም "ይህ በምድሪቱ ሁሉ ላይ ያለው
የሕዝቡ በደል[+] ነው" አለኝ::
7ከዚያም ከእርሳስ የተሠራው ክዳን ተነሣ፤
የኢፍ መስፈሪያ ውስጥ አንዲት ሴት ተቀ
ምጣ ነበር:: 8እርሱም፣ "ይህች ርኵሰት ናት"
ብሎ ወደ ኢፍ መስፈሪያ መልሶ አስገ
ባት፤ የእርሳሱንም ክዳን ወደ ቅርጫቱ አፍ
ገፍቶ ገጠመው::
9ከዚያም ወደ ላይ ተመለከትሁ፤ እነ
ሆም፣ ከፊቴ ሁለት ሴቶች ነበሩ፤ በክንፎቻ
ቸውም ነፋስ ነበር፤ ክንፎቻቸውም እንደ
ሽመላ ክንፎች ነበሩ፤ የኢፍ መስፈሪያው
ንም በምድርና በሰማይ መካከል አነሡት::
10ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረውንም መል
አክ፣ "ቅርጫቱን የሚወስዱት ወዴት ነው?"
አልሁት::
11እርሱም፣ "ቤት ሊሠሩለት ወደ ባቢ
ሎን[b] ምድር ይወስዱታል፤ በተዘጋጀም ጊዜ

5፥4 ዘሌ14፥34-45፤ምሳ3፥33፤ ዕን2፥9-11፤ ዘካ8፥17፤ሚል3፥5
5፥6 ሚክ6፥10
5፥8 ሚክ6፥11
5፥9 ዘሌ11፥19
5፥11 ዘፍ10፥10፤ ኤር29፥5፡28፤ ዳን1፥2
6፥1 ቍ5፤ 2ነገ2፥11
6፥2 ራእ6፥5
6፥3 ራእ6፥2
6፥5 ኢሱ3፥11፤ ሕዝ37፥9፤ማቴ 24፥31፤ራእ7፥1
6፥7 ኢሳ43፥6፤ ዘካ1፥8
6፥8 ሕዝ5፥13፤ 24፥13፤ዘካ1፥10

ወስደው በቦታው ያስቀምጡታል" አለኝ::

## አራቱ ሠረገሎች

6 እንደ ገናም ወደ ላይ ተመለከትሁ፤ እነሆ
አራት ሠረገሎች ከሁለት ተራራ መካ
ከል ሲወጡ አየሁ፤ ተራሮቹም የናስ ተራሮች
ነበሩ:: 2የመጀመሪያው ሠረገላ መጋላ፣
ሁለተኛው ዱሪ፤ 3ሦስተኛው አምባላይ፤ አራ
ተኛውም ዥጕርጕር ፈረሶች ነበሯቸው፤
ሁሉም ጠንካሮች ነበሩ:: 4እኔም ከእኔ ጋር
ይነጋገር የነበረውን መልአክ፣ "ጌታዬ ሆይ፤
እነዚህ ምንድን ናቸው?" አልሁት::
5መልአኩም እንዲህ አለኝ፤ "እነዚህ አራቱ
ቆመው ከነበሩበት ከምድር ሁሉ ጌታ ፊት
የወጡ የሰማይ መናፍስት[+] ናቸው:: 6የባለ
ዱሪ ፈረሶች ወደ ሰሜን፤ የባለ አምባላይ
ፈረሶች ወደ ምዕራብ[c] አገር፣ የባለ ዥንጕ
ርጕር ፈረሶች ወደ ደቡብ አገር ይወጣል::"
7ጠንካሮቹ ፈረሶች ሲወጡ፣ በምድር ሁሉ
ለመመላለስ አቈብቍበው ነበር:: እር
ሱም፣ "ወደ ምድር ሁሉ ሂዱ" አላቸው፤
እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ ሄዱ:: 8ከዚያም
ጮኾ እንዲህ አለኝ፤ "እነሆ፤ ወደ ሰሜን
አገር የሚወጡት፣ መንፈሴን በሰሜን
ምድር አሳርፈውታል::"

## ለኢያሱ የተደረገለት አክሊል

9*የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ*

[a]6 ከቍ7-11 ካለው ጭምር፣ የእህል መስፈሪያ ወይም ቍና ማለት ነው::
[+]6 ወይም *መምሰል*
[b]11 ዕብራይስጡ ሺናር ይለዋል::
[+]5 ወይም *ነፋሳት ሊሆን ይችላል::*
[c]6 ወይም *ከኋላቸው ፈረሶቹ እንደማለት ነው::*

ስፍራ የተጠቀሰው የመጽሐፍ ጥቅልል በፊቱና በጀርባው ላይ ተጽፎ በታል (ከሕዝ 2፥9-10፤ራእ5፥1 ጋር ያነጻጽሩ:: *የሚሰርቅ፤* ስምን ተኛውን ትእዛዝ ይተላለፋል (ዘፀ 20፥15):: *በሐሰት ወደሚምለው፤* 8፥17 ይመ:: እንዲህ ዐይነቱ ሰው ደግሞ ሦስተኛውን ትእ ዛዝ ይተላለፋል (ቍ4፤ ከዘፀ20፥7 ጋር ያነጻጽሩ):: በዚያን ወቅት መስረቅና ማታለል ዘወትር ይፈጸም ነበር፤ እንዲያውም ኀጢአ ትን ሁሉ ሊወክል ይችላል:: የይሁዳ ሕዝብ ግን ሕግን ሁሉ በመ ተላለፍ በድሉአል (ከያዕ2፥10 ጋር ያነጻጽሩ)::

5፥4፤ *ይገባል...ያጠፋል፤ ርግማኑን ያሳያል* (ቍ3):: የእግዚ አብሔር ቃል ተስፋን የሚሰጥም (ም4) ቢሆን በዚህ ስፍራ እንደ ተጠቀሰው የሚያስጠነቅቅ፣ ሁልጊዜ ዐላማውን ከዳር የሚያደርስ ነው (መዝ147፥15፤ከኢሳ55፥10-11፤ዕብ4፥12-13 ጋር ያነጻጽሩ)::

*5፥5-11፤* የዘካርያስ ሰባተኛው ራእይ ግፍ የሚሠሩ ግለ ሰቦች ብቻ ሳይሆኑ (ቍ14)፣ ኀጢአትን ሁልጊዜ የሚፈጽሙ ሁሉ ከምድሪቱ ይወገዳሉ::

5፥6፤ *የኢፍ መስፈሪያ፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ:: ይህ ዕቃ ለአጽንዖት ትልቅ ቢመስልም እንኳ ሰውን የሚይዝ አይ ደለም:: እንደ በራሪው የመጽሐፍ ጥቅልል ለራእዩ ሲባል ትልቅ ሆኖ የቀረበ ነው (ቍ12:: *በደል፤* ቍ8 ላይ "ርኵሰት" የሚለውን ይመ::

5፥7፤ *ሴት፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ፤ የሕዝቡ ርኵሰት ሴት ተብሎ በሰውኛ አገላለጽ ቀርቧል (ራእ17፥36ጋር ያነጻጽሩ):: ከዕብራይስጡ "ርኵሰት" (ቍ8) የሚለው ቃል በሴቴ ጾታ ነው::

5፥8፤ ርኵሰት፤ የግብረገብ፣ የሃይማኖትና የማኅበራዊ ክፋትን የሚያመለክት ቃል ሲሆን፣ አብዛኛውን ጊዜ የጽድቅ ተቃራኒ በመሆን ጥቅም ላይ ውሎአል (ምሳ13፥6፤ ሕዝ33፥12 ይመ):: የክፋት ምንጮች ሁሉ ይወገዳሉ (ከ2ተሰ 2፥6-8 ጋር ያነጻጽሩ)::

5፥9፤ *ሁለት ሴቶች፤* የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸው:: *ነፋስ፤* የእግዚአብሔር መሣሪያ ነው መዝ104፥3-4:: ክፋ ትን ማስወገድ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው::

5፥11፤ *ባቢሎን፤* ዘፍ10፥10 እና አማራጭ ትርጕሙን ይመ፤ ዘካ11፥2እና አማራጭ ትርጕሙን ይመ፤ ራእ17-18 ይመ:: ባቢሎን የምንዝርናና የክፋት ሁሉ ምድር ስትሆን፣ እስራኤል ግን የእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን የተመረጠች ምድር ናት:: የተስፋዪቱ ምድር ከኀጢአቷ ከነጻች በኋላ፣ "የተቀደሰችው ምድር" ተብላ ትጠራለች (2፥12)::

*6፥1-8፤* የዘካርያስ ስምንተኛውና የመጨረሻው ራእይ ነው:: ከመጀመሪያው ራእይ (1፥7-17) ጋር ይመሳሰላል፤ ነገር ግን የፈረሶቹ ቅደም ተከተልና መልክ የተለያየ ነው:: እንደ መጀመሪያው ራእይ ሁሉ ፣እግዚአብሔር የዓለምን ታሪክ እንደ ሚቈጣጠር ሆኖ ተገልጾአል:: እስራኤልን የሚጨቁኑ መንግሥ ታትን ድል ይነሣቸዋል::

6፥1፤ *አራት ሠረገሎች፤* መለኮታዊ ፍርድን የሚያከናውኑ መናፍስት ናቸው (ቍ5):: *ከሁለት ተራራ፤* ምናልባት የጽዮንና የደብረዘይት ተራሮች ሲሆኑ የቄድሮንም ሸለቆ በእነዚህ ሁለት ተራሮች መካከል ይገኛል:: *የናስ፤* የፍርድ ምልክት ሳይሆን አይ ቀርም (ከዘኍ21፥9 ጋር ያነጻጽሩ)::

6፥2-3፤ *መጋላ... ዱሪ... አምባላይ... ዥጕርጕር፤* ፈረሶቹ በም ድር ላይ የሚፈጸሙ መለኮታዊ ፍርዶችን የሚያመለክቱ ሊሆኑ ይች ላሉ (የቍ8 ማብ ይመ)፤ ራእ6፥1-8እና የራእ 6፥2 ማብ ይመ::

6፥4፤ *እነዚህ፤* ሠረገሎቹንና ፈረሶቻቸውን የሚያመለክት ነው::

6፥5፤ *አራቱ... መናፍስት፤* የቍ1ማብ ይመ:: *ከምድር ሁሉ ጌታ፤* የ4፥14 ማብ ይመ::

6፥8፤ *ሰሜን አገር፤* በቀዳሚነት ባቢሎንን ያመለክታል፤ በተጨማሪም የእስራኤል ጠላቶች ፓሌስቲናን ለመውረር የሚ መጡበትን አቅጣጫ ያሳያል (የ2፥6 ማብ ይመ):: *መንፈሴን፤* የሰው መንፈስ ሳይሆን አይቀርም፤ በዚህ መሠረት የክፍሉ ሐሳብ ወደ ሰሜን የተላኩት መላእክት፣ ጠላትን በማሸነፍ የእግዚአብሔ ርን መንፈስ አሳርፈዋል፤ ቍጣውንም አብርደዋል ማለት ነው (ከመክ10፥4 ጋር ያነጻጽሩ):: የእግዚአብሔር ቍጣ በእስራ ኤል ጠላቶች ላይ እንደ ነደደ የሚናገረውን 1፥15 ይመ::

*6፥9-15፤* አራተኛውና አምስተኛው ራእይ ፣ሊቀ ካህኑንና አገር አስተዳዳሪውን የሚመለክት ነው:: ዘካርያስ የሁለቱን ራእ

እኔ መጣ፤ [10]"ከባቢሎን ከመጡት ምርኮኞች
ከሔልዳይና ከጦብያ ከዮዳኤም ወርቅና ብር
ውሰድ፤ በዚያው ቀን ወደ ሶፎንያስ ልጅ ወደ
ኢዮስያስ ቤት ሂድ:: [11]ወርቁንና ብሩን ወስ
ደህ አክሊል ሥራ፤ በኢዮሴዴቅ ልጅ በሊቀ
ካህኑ በኢያሱ ራስ ላይም አድርገው::[12]ለእ
ርሱም እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል
ብለህ ንገረው፤ 'እነሆ፤ ስሙ ቅርንጫፍ
የተባለው ሰው ይህ ነው፤ እርሱም በቦታው
ይንሰራፋል፤ የእግዚአብሔርንም ቤተ መቅ
ደስ ይሠራል:: [13]የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስ የሚሠራው እርሱ ነው፤ ክብርን
ይጐናጸፋል፤ በዙፋኑ ተቀምጦ ይገዛል፤ በዙ
ፋኑም ላይ ካህን ይሆናል፤ በሁለቱም መካ
ከል ስምምነት ይኖራል:: [14]አክሊሉም ለሔ
ሌምና' ለጦብያ፣ ለዮዳኤና ለሶፎንያስ ልጅ
ለሔን[ፐ] በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
ውስጥ መታሰቢያ ይሆናል:: [15]እነዚያ በሩቅ
ያሉት መጥተው የእግዚአብሔር ቤተ መቅ
ደስ ሲሠራ ያግዛሉ፤ እናንተም እግዚአ
ብሔር ጸባኦት እንደ ላከኝ ታውቃላችሁ::
ስለምላካችሁ ለእግዚአብሔር በጥንቃቄ ብትታ
ዘዙ ይህ ይሆናል::"

## ፍትሕና ምሕረት የተወደደ ነው

**7** ዳርዮስ በነገሠ በአራተኛው ዓመት፣
ካሴሉ በተባለው በዘጠነኛው ወር፣ በአ
ራተኛው ቀን የእግዚአብሔር ቃል ወደ
ዘካርያስ እንዲህ ሲል መጣ፤ [2]የቤቴል ሰዎች
እግዚአብሔርን ለመለመን ሳራሳርንና ሬጌሜ
ሌክን አብረዋቸው ከነበሩት ሰዎች ጋር
ላኩ፤ [3]እነርሱም የእግዚአብሔር ጸባኦት
ቤት ካህናትና ነቢያት፣ "ብዙ ዓመት እንዳ
ደረግሁት፣ በአምስተኛው ወር ማዘንና መጾም
ይገባኛልን?" ብለው ጠየቁ::
[4]ከዚያም የእግዚአብሔር ጸባኦት ቃል
እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ [5]"የምድሩን ሕዝብ
ሁሉና ካህናቱን እንዲህ በላቸው፤ 'ባለፉት
ሰባ ዓመታት በአምስተኛውና በሰባተኛው
ወር የጾማችሁትና ያዘናችሁት በእርግጥ
ለእኔ ነበርን? [6]ትበሉና ትጠጡ የነበረውስ
ለራሳችሁ አይደለምን? [7]ኢየሩሳሌምና በዙ
ሪያዋ ያሉ ከተሞች በሰላምና በብልጽግና
ላይ ሳሉ፣ የደቡብና የምዕራብ ኰረብቶች
ግርጌ የሰው መኖሪያም በነበሩበት ጊዜ፣
እግዚአብሔር በቀደሙት ነቢያት የተናገ
ረው ቃል ይህ አልነበረምን?' "
[8]የእግዚአብሔር ቃል እንደ ገና ወደ ዘካር
ያስ እንዲህ ሲል መጣ፤ [9]"እግዚአብሔር
ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ 'እውነተኛ ፍትሕ አስ
ፍኑ፣ እርስ በርሳችሁ ምሕረትና ርኅራኄን
አድርጉ፤ [10]መበለቲቱን ወይም ድኻ አደ
ጉን፣ መጻተኛውን ወይም ድኻውን አታስ
ጨንቁ፤ በልባችሁም አንዳችሁ በአንዳችሁ
ላይ ክፉ አታስቡ::'

6፥10 ዕዝ7፥14-16፤ኤር28፥6
6፥11 1ዜና 6፥15፤ዕዝ2፥2፤3፥2፤ መዝ21፥3፤ዘካ3፥1
6፥12 ዕዝ3፥8-10፤ ኢሳ4፥2፤ሕዝ17፥22፤ ዘካ4፥6፥9
6፥13 መዝ110፥4
6፥14 ዘፀ28፥12
6፥15 ኢሳ58፥12፤ 60፥10፤ኤር7፥23፤ዘካ 2፥9-11፤3፥7
7፥1 ዕዝ5፥1፤ ነህ1፥1
7፥2 ኤር26፥19፤ ሐጌ2፥10-14፤ ዘካ8፥21
7፥3 2ነገ25፥9፤ ኤር52፥12-14፤ ዘካ12፥12-14
7፥5 2ነገ25፥25፤ ኢሳ58፥5፤ዳን9፥2
7፥6 ኢሳ43፥23
7፥7 ኢሳ1፥11-20፤ ኤር17፥26፤22፥21፤ 44ም4-5፤ዘካ1፥4
7፥9 ዘጻ22፥1፤ ኤር22፥3፤42፥5፤ ዘካ8፥16
7፥10 ዘፀ22፥21: 22፤ዘሌ25፥17፤ ኢዮ35፥8፤ ኢሳ1፥17:23

'14 ሲርያክ፤ ዕብራይስጡ ሂሊም ይላል::
[ፐ]14 ወይም ርኅሩኁ እንደማለት ነው::

---

ዮች መልእክት ከመሲሑ የንጉሥነትና የክህነት አገልግሎት ጋር ያዛምደዋል::

*6፥9፤* የትንቢት ንግርን ያስተዋውቃል (4፥8፤7፥4:8፤8፥1:18፤ እንዲሁም የ1፥1ማብ ይመ)::

6፥10፤ *ወርቅና ብር፤* ለቤተ መቅደስ የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው (ከዕዝ6፥5፤ከሐጌ2፥8) ጋር ያነጻጽሩ::

6፥11፤ *አክሊል፤* በዕብራይስጡ ይህ ቃል የሊቀ ካህናቱን የራስ ጥምጥም የሚያመለክት ሳይሆን፣ ጌጠኛውን ዘውድ የሚያሳይ ነው (ከራእ19፥12 ጋር ያነጻጽሩ):: ሊቀ ካህናቱ ንጉሣዊ የሆነውን ዘውድ መጫኑ፣ ስለ መሲሑ ንጉሣዊ ክህነት የተነገረ ውን ትንቢት ግብና ፍጻሜ የሚያመለክት ነው (ቍ12-13 ይመ፤ ከመዝ 10፥4፤ዕብ7፥13 ጋር ያነጻጽሩ)::

6፥12፤ *እነሆ...ሰው ይህ ነው፤* በዮሐ19፥5 ላይ ጲላጦስ ስለ ኢየሱስ ከተናገረው ጋር ያነጻጽሩ:: *ቅርንጫፍ፤* የ3፥8 ማብ ይመ:: የአራማይኩ ትርጕም (የአራማይኩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አብራሂ ሐሳብ ትርጕም ነው)፣ የኢየሩሳሌሙ ታልሙድ (የሃይማኖታዊ ትምህርት ስብስብ ነው)እንዲሁም ሚድራሽ (የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተተነተነበት ነው) እንደሚያስረዳው፣ ቀደ ምት አይሁድ ይህ ክፍል ስለ መሲሑ የተነገረ ነው የሚል እም ነት ነበራቸው:: *ቤተ መቅደስ፤* ከኢሳ2፥2-3፤ሕዝ40-43፤ሐጌ 2፥6 ጋር ያነጻጽሩ::

6፥13፤ *በዙፋኑ፤* 2ሳሙ7፥16፤ኢሳ9፥7 እና ማብ ይመ፤ ሉቃ1፥32 ይመ:: *በዙፋኑም ላይ ካህን ይሆናል፤* ከዳዊት ዘር የሆነው የሚመጣው ንጉሥ ካህንም ነው:: *በሁለቱም፤* የንጉሣዊ ውንና የክህነት አገልግሎቱን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል:: እን ዲህ ዐይነቱ ጥምር አገልግሎት በእስራኤል የተለመደ አይደ ለም:: ከዚህም የተነሣ በቁምራን የነበሩት ሃይማኖተኞች ("በሁ ለቱ ኪዳናት መካከል ያለው ዘመን" የሚለውን ርእስ ይመ)፣ አን ደኛው ሊቀ ካህናት የሆነ ሌላው ደግሞ ከዳዊት ዘር የሆነ ሁለት ዐይነት መሲሖችን ይጠባበቁ ነበር:: እውነታው ግን ሁለ ቱም አገልግሎቶች በአንዱ መሲሕ የሚከናወኑ መሆናቸው ነው (ከመዝ 110፤ከዕብ7 ጋር ያነጻጽሩ)::

6፥14፤ *ለሔን፤* "ጸጋን የተሞላ" ማለት ነው (አማራጭ ት ርጕሙን ይመ):: ኢዮስያስ ለሰዎች ከሚያሳየው በጎነት የተነሣ የተሰጠው የክብር ስም ሊሆን ይችላል (ቍ10 ይመ)::

6፥15፤ *በሩቅ ያሉት.....ያግዛሉ፤* ከኢሳ60፥47 ጋር ያነጻጽሩ::

7፥1፤ *በአራተኛው ዓመት... በዘጠነኛው ወር፣ በአራተ ኛው ቀን፤* ታኅሣሥ 7ቀን 518 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው፤ ስምንቱን ራእዮች ካየበት ሌሊት ሁለት ዓመት ከመሙላቱ በፊት ማለት ነው (የ1፥7ማብ ይመ)::

7፥3፤ *ነቢያት፤* ዘካርያስንም ጨምሮ ማለት ነው:: *ብዙ ዓ መት፤* "ባለፉት ሰባ ዓመታት" ማለት ነው ቍ5:: *በአምስተ ኛው ወር....መጾም፤* የ8፥19ማብ ይመ:: 7፥4፤ *ይገባኛልን?፤* በአጠቃላይ የቤቴልን ሕዝብ ያመለክታል::

*7፥4-7፤* በስብስግብነትና እውነተኛ ባለመሆን በመጾማቸው የተሰጣቸው ተግሣጽ::

*7፥4:8፤* የ6፥9ማብ ይመ::

7፥5፤ *በአምስተኛውና በሰባተኛው ወር የጾማችሁት፤* የ8፥19 ማብ ይመ:: *ሰባ ዓመታት፤* 1፥12 እና ማብ ይመ:: ይህ ጾም ለኢየሩሳሌምንና ለቤተ መቅደሱ መፍረስ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የሚደረግ ነው (የ8፥19 ማብ ይመ)፤ ሰባው ዓመት ከ580 ዓ.ቅ.ክ ጀምሮ የሚቈጠር ነው፤ በዚህ ጊዜ ግን ሥልሳ ስምንት ዓመት ሆኖታል፤ ሰባ የተባለው ተጠጋግቶ ነው::

7፥6፤ *ለራሳችሁ፤* ከኢሳ1፥11-17፤58፥1-7:13-14 ጋር ያነጻጽሩ::

7፥7:12፤ *በቀደሙት ነቢያት፤* የ1፥4 ማብ ይመ::

7፥7፤ *የምዕራብ ኰረብቶች፤* ወደ ሜድትራኒያን የሚያቈ ለቍለው ነው:: *የደቡብና የምዕራብ፤* የዘፍ 12፥9 ማብ ይመ::

7፥9-10፤ ለኪዳኑ የሚገባ ኑሮ ለመኖር አራቱ መስፈርቶች ማኅበራዊ፣ ግብረ ገባዊና ሥነ ምግባራዊ ትእዛዞችን ያጠቃልላል::

7፥9፤ *ፍትሕ፤* ማንኛውም ኀብረተ ሰብ በሥርዐት የሚተ ዳደርበት ነው (ከ8፥16 ጋር ያነጻጽሩ፤ ኢሳ42፥1:4፤ሚክ6፥8 ይመ):: *ምሕረትና፤* ወይም፣ "እውነተኛ ፍቅር" ማለት ነው (ከሆሴ 10፥12፤ 12፥6 ጋር ያነጻጽሩ):: *ርኅራኄን፤* የ1፥16ማብ ይመ::

7፥10፤ *አታስጨንቁ፤* ጭቈና በብሉይ ኪዳን ተደጋግሞ ተወግዞአል (አሞ2፥6-8፤4፥1፤5፥11-12:21-24፤8፥46ይመ):: *መበ ለቲቱን...ድኻ አደጉን መጻተኛውን...ድኻውን፤* መጽሐፍ ቅዱስ ለእንደዚህ ዐይነት ሰዎች የሚሰጠውን ትኵረት በዘዳ10፥18፤ኢሳ 1፥17እና ማብ፤ኤር 5፥28፤ያዕ1፥27፤1 ዮሐ3፥16-18ይመ:: በጥንት ጊዜ በቅርብ ምሥራቅ የነበሩ መልካም ነገሥታት ችግረኛውንና የተጨቈነውን የመርዳት ኀላፊነት ነበረባቸው:: *አንዳችሁ በአንዳ*

11“እነርሱ ግን መስማት አልፈለጉም፤
በእልኸኝነት ጀርባቸውን አዞሩ፤ ጆሮአቸው
ንም ደፈኑ:: 12ልባቸውን እንደ ባልጩት
አጠነከሩ፤ እግዚአብሔር ጸባኦት በቀደ
ሙት ነቢያት በኩል በመንፈሱ የላከውን
ቃል ወይም ሕግ አልሰሙም፤ ስለዚህ እግ
ዚአብሔር ጸባኦት እጅግ ተቈጣ::
13‘ ‘ስጠራቸው አልሰሙም፤ ስለዚህ ሲጠ
ሩኝ አልሰማም’ ይላል እግዚአብሔር ጸባ
ኦት::” 14በማያውቋቸው በባዕዳን አሕዛብ
መካከል በዐውሎ ነፋስ በተንኳቸው፤ ከእ
ነርሱ በኋላ ማንም እስከማይመላለስባትና እስ
ከማይሄድባት ድረስ ምድሪቱ ባድማ ሆነች፤
መልካሚቱን ምድር ባድማ ያደረጓት በዚህ
ሁኔታ ነው::’ ”

## እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ለመባረክ ቃል ገባ

8 እንደ ገናም የእግዚአብሔር ጸባኦት ቃል
እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ 2እግዚአ
ብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ “ስለ ጽዮን
እጅግ ቀንቻለሁ፤ ስለ እርሷም በቅናት ነድ
ጃለሁ::”
3እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ “ወደ
ጽዮን እመለሳለሁ፤ በኢየሩሳሌም እኖራለሁ፤
ኢየሩሳሌምም የእውነት ከተማ ትባላለች፤
የእግዚአብሔር ጸባኦት ተራራም ቅዱስ ተራራ
ይባላል::”
4እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
“ሽማግሌዎችና አሮጊቶች እንደ ገና በኢ
የሩሳሌም አደባባይ ይቀመጣሉ፤ እያንዳንዳ
ቸውም ከዕድሜአቸው ብዛት የተነሣ ምር
ኩዝ ይይዛሉ:: 5የከተማዪቱም አደባባዮች
እዚያ በሚጫወቱ ወንዶችና ሴቶች ልጆች
ይሞላሉ::”
6እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
“በዚያን ጊዜ ይህ ለቀረው የእስራኤል ሕዝብ
አስደናቂ መስሎ ሊታይ ይችላል፤ ለእኔ
ግን አስደናቂ ሊሆን ይችላልን?” ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት::
7እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ “ሕዝ
ቤን ከምሥራቅና ከምዕራብ አገር እታደጋ
ለሁ:: 8በኢየሩሳሌም እንዲኖሩ መልሼ አመ
ጣቸዋለሁ፤ እነርሱ ሕዝቤ ይሆናሉ፤ እኔም በጽ
ድቅና በታማኝነት ለምሳካቸው እሆናለሁ::”
9እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ “የእ
ግዚአብሔር ጸባኦት ቤት መሠረት ሲጣል፣
በዚያ የነበሩ ነቢያት የተናገሩትን ቃል
አሁን የምትሰሙ ሁሉ የእግዚአብሔርን
ቤተ መቅደስ ለመሥራት እጃችሁን አበ
ርቱ:: 10ከዚያ በፊት ለሰው ደመወዝ፣ ለእ
ንስሳም ኪራይ አይከፈልም ነበር፤ ጠላት
በመኖሩም ማንም ሥራውን በሰላም ማከና
ወን አልቻለም፤ እያንዳንዱ ሰው በባልንጀራው
ላይ እንዲነሣ አድርጌ ነበርና:: 11አሁን ግን
ቀድሞ እንዳደረግሁት በዚህ በቀረው ሕዝብ
ላይ አላደርግም” ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት::
12“ዘሩ ጥሩ ሆኖ ይበቅላል፤ ወይኑ ፍሬ
ውን ያፈራል፤ ምድሪቱ አዝመራዋን ታበረ
ክታለች፤ ሰማያትም ጠላቸውን ይሰጣሉ፤
እነዚህን ሁሉ ነገሮች ለቀሪው ሕዝብ ርስት
አድርጌ እሰጣለሁ:: 13የይሁዳ ቤትና የእስራ
ኤል ቤት ሆይ፤ በአሕዛብ መካከል የርግ
ማን ምሳሌ ነበራችሁ፤ አሁን ግን አድናችኋ

7፥11 ኢሳ9፥9፤ ኤር5፥3፤8፥5፤11፥10፤ 17፥23፤32፥33፤ ሕዝ5፥6
7፥12 ነህ9፥29፤ ኤር5፥3፤17፥1፤ 42፥21፤ሕዝ11፥19፤ ዳን9፥12
7፥13 ምሳ1፥28፤ ኢሳ1፥15፤ኤር7፥27፤ ኤር11፥11፥14፥12፤ ሰቆ3፥44፤ሕዝ20፥31፤ ሚክ3፥4
7፥14 ዘሌ26፥33፤ ዘዳ4፥27፤28፥64-67፤መዝ44፥11፤ ኢሳ33፥8፤ኤር 7፥34፤23፥19፤ 44፥6፤ሕዝ 12፥19
8፥2 ኢዩ2፥18
8፥3 መዝ15፥2፤ ኢሳ1፥26፤48፥1፤ 52፥8፤ኤር26፥18፤ 33፥16፤ኢዩ3፥21፤ ዘካ1፥16፤2፥10፤ ሚክ4፥1
8፥4 ኢሳ65፥20
8፥5 ኤር30፥20፤ 31፥13
8፥6 መዝ 128፥23፤126፥1-3፤ ኤር32፥17:27
8፥7 መዝ107፥3፤ ኢሳ11፥11፤43፥5
8፥8 ኢሳ51፥16፤ ኤር11፥4፤31፥24፤ ሕዝ11፥12-20፤ 36፥28፤37፥12፤ ዘካ2፥11፤10፥6:10፤ ዕን8፥108፥9፤ ዕዝ 3፥11፤5፥1፤ ሐጌ2፥4
8፥10 2ዜና15፥5፤ ኢሳ5፥10፤ሐጌ1፥6
8፥11 ኢሳ12፥1
8፥12 ዘፍ27፥28፤ መዝ65፥13፤67፥6፤ 85፥12፤ኢሳ60፥21፤ ሆሴ2፥21፤ኢዩ 2፥22፤አብ1፥17
8፥13 ቍ9፤ዘፍ12፥2፤ዘኍ5፥27፤ ዘዳ13፥15፤መዝ48፥8፤102፥8፤ኤር42፥18፤ኢዩ2፥14፤ሐጌ2፥5

ችሁ ላይ ክፉ አታስቡ፤ 8፥17ይመ::

7፥11፤ *አልፈለጉም፣* ከምርኮ በፊት የነበሩ አባቶች፣ በቍ12፤ “ቀደምት ነቢያት” ከሚለው ሐረግ ጋር ያነጻጽሩ:: *በእልኸኝነት ጀርባቸውን አዞሩ፤* ዘዳ9፥6:13:27 ይመ:: *ጆሮአቸውንም ደፈኑ፤* መዝ58፥4፤ኢሳ6፥10 እና ማብ ይመ፤ ከኢሳ 33፥15ጋር ያነጻጽሩ::

7፥12፤ *እንደ ባልጩት፤* ሕዝ3፥8-9 ይመ:: *በመንፈሱ የላከውን ቃል፤* ነቢያት የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩት በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት ነው (ከነህ9፥30፤2ጴጥ1፥21ጋር ያነጻጽሩ):: *እጅግ ተቈጣ፤* 1፥2:15 ይመ::

7፥13፤ የ1፥3 ማብ ይመ::

7፥14፤ *በዐውሎ ነፋስ፤* ምሳ1፥27፤ኢሳ40፥24፤ ሆሴ4፥19 ይመ:: *በተንኳቸው፤* ይህ ቃል ኪዳኑን በመተላለፍ ከሚደርሱት ርግማኖች መካከል አንዱ ነው (ዘዳ28፥36-37:64-68 ይመ፤ የዘዳ 28፥64 ማብ ይመ):: *ምድሪቱ ባድማ፤* ዘዳ28፥41-42: 45-52 ይመ:: *መልካሚቱን ምድር፤* ከመዝ106፥24፤ከኤር3፥19 ጋር ያነጻጽሩ:: *በዚህ ሁኔታ ነው፤* ከኀጢአታቸው የተነሣ ማለት ነው::

8፥1-23፤ “የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል” በሚል ፀረፍተ ነገር የሚጀመሩ ቍ2:3:4:6:7:9:14: 18:20: 23 ዐሥር የበረከት ተስፋዎች ይገኙበታል::

8፥1:18፤ የ6፥9 ማብ ይመ::

8፥2፤ *ቀንቻለሁ፤* 1፥14ይመ እንዲሁም የዘፀ20፥5 ማብ ይመ::

8፥3፤ *እመለሳለሁ፤* 1፥3 እና ማብ ይመ ፤1፥16 ይመ:: *እኖራለሁ፤* የ2፥10ማብ ይመ:: *የእውነት ከተማ፤* ከቍ16ጋር ያነጻጽሩ፤ ኢሳ1፥26 እና ማብ ይመ:: *ቅዱስ ተራራ፤* ከ14፥20-21 ማብ ጋር ያነጻጽሩ::

8፥4-5፤ ኢሳ11፥6-9 እና ማብ ይመ፤65፥20-25ይመ::

8፥6:11-12 *ለቀሪው፤* የኢሳ1፥9፤10፥20-22 ማብ ይመ::

8፥6፤ *ለእኔ ግን አስደናቂ ሊሆን ይችላልን?* ዘፍ18፥14 እና ማብ፤ኤር32፥17:27ይመ::

8፥7፤ *ሕዝቤን...እታደጋለሁ፤* ከምርኮ፣ ከባርነትና ከመበተን ማለት ነው (ከኢሳ11፥11-12፤43፥5-7፤ ከኤር30፥7-11፤ 31፥7-8 ጋር ያነጻጽሩ):: *ከምሥራቅና ከምዕራብ አገር፤* በቀመ “ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያዋ” ማለት ሲሆን፣ ይህም ሕዝቡ ካለበት ስፍራ ሁሉ ማለት ነው (ከመዝ50፥1፤ 113፥3፤ሚል1፥11 ጋር ያነጻጽሩ)::

8፥8፤ *እነርሱ ሕዝቤ ይሆናሉ፤ እኔም...አምላካቸው እሆናለሁ፤* የጠበቀ የቃል ኪዳን ግንኙነትንና አንድነትን የሚያመለክት ቃል ነው (13፥9፤ ዘፍ17፥7 እና ማብ፤ ዘፀ6፥7፤29፥45-46፤ ዘሌ 11፥45፤22፥33፤25፥38፤26፥12እና ማብ፤26፥45፤ዘኍ15፥41፤ ዘዳ29፥13፤ኤር24፥7፤31፥33፤32፥38፤ሕዝ34፥30-31፤36፥28፤37፥27፤ ሆሴ1፥9-10፤2፥23፤2ቆሮ6፥16፤ዕብ8፥10፤ራእ21፥3 ይመ):: *በጽድቅና በታማኝነት፤* የይሁዳ ሕዝብ ወደ ኪዳኑ በረከት መመለሱ፣ በእግዚአብሔር ጽድቅና ታማኝነት በእግዚአብሔር በመደገፍ ላይ የተመሠረተ ነው::

8፥9፤ *ነቢያት፤* ሐጌንና 1፥1 ዘካርያስን1፥1 ጨምሮ ማለት ነው (ከዕዝ5፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ):: *እጃችሁን አበርቱ፤* ቍ13ይመ:: ቃሉ በዕብራይስጥ፣ “በርቱ” ማለት ነው (መሳ7፥11ይመ)::

8፥10፤ *ከዚያ በፊት፤* የቤተ መቅደሱ መሠረት ከመጣሉ አስቀድሞ ማለት ነው (ቍ9 ይመ):: *ደመወዝ...አይከፈልም፤* ሐጌ 1፥6-11፤2፥15-19ይመ:: *ጠላት፤* ለምሳሌ፡ ሳምራውያንን ማለት ነው ዕዝ 4፥1-5

8፥11፤ *አሁን ግን፤* ተስፋ የሚያስቈርጡ ምክንያቶች ተወግደዋል፤ አሁን እግዚአብሔር የሚያበረታቱ ሁኔታዎችን ያዘጋጃል::

8፥12፤ ከሐጌ1፥10-11ጋር ያነጻጽሩ:: የዚህ ክፍል ተቃራኒ እንደሚፈጸም እግዚአብሔር በሐጌ2፥19 ላይ ተናግሮአል:: የሆድና የምድር ፍሬ በረከቶች እግዚአብሔርን ለሚታዘዙ የተሰጡ የቃል ኪዳን ተስፋዎች ናቸው (ዘሌ26፥3-10፤ ዘዳ28፥11-12ይመ፤ ከሕዝ 34፥25-27 ጋር ያነጻጽሩ)::

8፥13፤ *በአሕዛብ መካከል የርግማን ምሳሌ፤* በዘዳ28፥15-68 ከተዘረዘሩት ቃል ኪዳኑን ከመተላለፍ የተነሣ ከሚመጡ ርግማ

ለሁ፤ እናንተም በረከት ትሆናላችሁ። አት
ፍሩ፤ ነገር ግን እጃችሁን አበርቱ።”
14*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
“አባቶቻችሁ ባስቈጡኝ ጊዜ ያላንዳች ሐዘ
ኔታ ጥፋት ላመጣባችሁ እንደ ወሰንሁ፣”
ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት፤ 15“አሁን ደግሞ
ለኢየሩሳሌምና ለይሁዳ መልካም ነገርን
ላደርግ ወስኛለሁ፤ አትፍሩ። 16ልታደርጓ
ቸው የሚገባችሁ ነገሮች እነዚህ ናቸው፤
እርስ በርሳችሁ እውነትን ተነጋገሩ፤ በአደ
ባባያችሁም እውነትንና ትክክለኛ ፍርድን
አስፍኑ፤ 17በባልንጀራችሁ ላይ ክፋትን በል
ባችሁ አታውጠንጥኑ፤ በሐሰት መማልን
አትውደዱ፤ እነዚህን ሁሉ እጸየፋለሁ”
ይላል *እግዚአብሔር*። 18እንደ ገናም የ*እግ
ዚአብሔር* ጸባኦት ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ፤ 19*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ
ይላል፤ “የአራተኛው፣ የአምስተኛው፣ የሰባ
ተኛውና የዐሥረኛው ወር ጾሞች ለይሁዳ
ቤት የደስታ፣ የተድላና የሐሤት በዓላት
ይሆናሉ፤ ስለዚህ እውነትንና ሰላምን
ውደዱ።”

20*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
“ብዙ ሕዝቦችና የብዙ ከተሞች ነዋሪዎች
ገና ይመጣሉ፤ 21የአንዲቱ ከተማ ነዋሪዎ
ችም፣ ‘*እግዚአብሔርን* ለመለመን *እግዚአ
ብሔር* ጸባኦትን ለመፈለግ፣ ኑ፤ በፍጥነት
እንሂድ፤ እኔም ራሴ እሄዳለሁ’ እያሉ ወደ
ሌላይቱ ከተማ ይሄዳሉ። 22ብዙ ሕዝብና
ኀያላን መንግሥታትም *እግዚአብሔር* ጸባ
ኦትን ለመፈለግና ለመለመን ወደ ኢየሩ
ሳሌም ይመጣሉ።” 23*እግዚአብሔር* ጸባኦት
እንዲህ ይላል፤ “በእነዚያም ቀናት ከየ
ወገኑና ከየቋንቋው ዐሥር ሰዎች የአንድን
አይሁዳዊ ልብስ ዘርፍ አጥብቀው በመያዝ፣
“‘*እግዚአብሔር* ከእናንተ ጋር እንዳለ ሰም
ተናልና አብረን እንሂድ’” ይሉታል።

## በእስራኤል ጠላቶች ላይ የተወሰነ ፍርድ

9 የ*እግዚአብሔር* ቃል ንግር በሴድራክ
ምድር ላይ ይወርድበታል፤
በደማስቆም ላይ ያርፍበታል፤
የሰዎችና የእስራኤል ነገዶች ሁሉ ዐይን፣
*በእግዚአብሔር* ላይ[1] ዐርፎአልና።
2ደግሞም በአዋሳኟ በሐማት፣
ጥበበኞች ቢሆኑም እንኳ በጢሮስና በሲ
ዶና ላይ ያርፍባቸዋል።
3ጢሮስ ለራሷ ምሽግ ሠርታለች፤
ብሩን እንደ ዐፈር
ወርቁንም እንደ መንገድ ላይ ትቢያ ቈልላለች።
4ጌታ ግን ሀብቷን ይወስዳል፤
በባሕር ያላትንም ኀይል ይደምስሳል፤
እርሷም በእሳት ፈጽማ ትጠፋለች።

*[1] ወይም ደማስቆ የእግዚአብሔር ዐይን በሰው ሁሉ ላይ ያያልና፤ በእስራኤል ነገዶች ላይ እንደሆነው ሁሉ።*

8፥14 ሕዝ24፥14
8፥15 ቍ13፤ ኤር29፥11፤31፥28፤32፥42፤ሚክ7፥18-20
8፥16 መዝ15፥2፤ ኤር33፥16፤ ሕዝ18፥8፤ 45፥9፤አሞ5፥15፤ ዘካ7፥9፤ኤፌ4፥25
9፥1 ኢሳ17፥1፤ አሞ1፥5
9፥2 ዘፍ10፥15፤ ኤር49፥23፤ ሕዝ28፥1-19
9፥3 ኢዮ27፥16፤ ሕዝ28፥4
9፥4 ኢሳ23፥1:11፤ኤር25፥22፤ ሕዝ26፥3-5

ኖች መካከል አንዱ ነው፤ (ዘዳ28፥37 ይመ) (ከኤር 24፥9፤ 25፥18 ጋር ያነጻጽሩ። *የይሁዳ ቤትና የእስራኤል ቤት፤* ሕዝቡ ዐርነትና በረከት ያገኛሉ (ከኤር31፥1-31፤ ከሕዝ37፥15-28 ጋር ያነጻጽሩ)። *በረከት፤* ቍ 20-23 ይመ፤ ከዘፍ12፥2 ጋር ያነጻጽሩ። *እጃችሁን አበርቱ፤* የቍ 9 ማብ ይመ።

*8፥14-17፤* ቍ 14-15 ሕዝቡን በማደስ ውስጥ እግዚአብሔር ምሕረትንና በረከትን በመስጠት፣ ያለውን ልዩ ድርሻ ያመለክታል፤ ቍ 16-17 ደግሞ የሕዝቡን ኀላፊነት ያሳያል።

8፥14፤ *አባቶቻችሁ ባስቈጡኝ ጊዜ፤* የ1፥2 ማብ ይመ።

8፥15፤ *መልካም ነገርን ላደርግ፤* ቍ 12-13 ይመ።

8፥16-17፤ 7፥9-10 ይመ። ከእግዚአብሔር ጋር የቃል ኪዳን ግንኙነት ያላቸው ሰዎች፣ ሊኖራቸው የሚገባውን ግብረ ገባዊና ሥነ ምግባራዊ ባሕርይ አጠቃሎ የያዘ ነው።

8፥16፤ *በአደባባያችሁም፤* በቀጥታ፣ “በር” ማለት ነው (ዘፍ 19፥1 እና ማብ ይመ፤ 2ሳሙ18፥24 ይመ)።

8፥17፤ *በሐሰት መማልን፤* ራስን ማታለል ነው የ5፥3 ማብ ይመ። *እነዚህን ሁሉ እጸየፋለሁ፤* በምሳ 6፥16-19 እግዚአብሔር የሚጠላቸው ሰባት ነገሮች ተዘርዝረዋል፤ ከእነርሱ መካከል ሦስቱ ቍ 16-17 ባለው ክፍል ውስጥ ይገኛሉ፤ እነዚህም፣ “ሐሰተኛ ምላስ” “ክፋትን የሚያውጠነጥን ልብ” እንዲሁም፣ “በውሸት ላይ ውሸት የሚጨምር ሐሰተኛ ምስክር” ናቸው።

8፥19፤ 7፥2-6 ይመ። *የአራተኛው፤* የኢየሩሳሌም ቅጥር በናቡከደናፆር የፈረሰበትን ዕለት ለማሰብ በሰቈቃ የሚጾም ጾም ነው (2ነገ25፥3-4፤ኤር39፥2፤52፥6-7)። *የአምስተኛው፤* ቤተ መቅ ደሱና ሌሎች ታላላቅ ሕንጻዎች የተቃጠሉበት ዕለት የሚታሰብ በት ነው (2ነገ25፥8-10፤ኤር52፥12-14)። *የሰባተኛውና፤* ጎዶልያስ የተገደለበት ዕለት የሚታሰብበት ነው (2ነገ25፥22-25፤ኤር41፥1-3)። *የዐሥረኛው፤* ናቡከደናፆር በመጀመሪያ ኢየሩሳሌምን የከበ በበት ዕለት በጥልቅ ሐዘን የሚታወሰበት ቀን ነው (2ነገ25፥1፤ ኤር39፥1፤ 52፥4፤ሕዝ24፥1-2)። *የሐሤት በዓላት፤* ከኢሳ65፥18-19፤ ከኤር 31፥10-14 ጋር ያነጻጽሩ።

*8፥20-23፤* የአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የመመለስ ፍላጎታ ቸው የተገለጠበትን ተመሳሳይ ትንቢት 2፥11 እና ማብ ይመ፤ ኢሳ2፥24፤ ከሚክ4፥1-5 ይመ።

8፥22፤ *ኀያላን፤* ወይም፣ “ብዙ” ማለት ነው (ዘፀ1፥9 እንደ ተጠቀሰው ኢሳ53፥12 አግራዊ ትርጕሙን ይመ)። የአሕዛብን መባረክ አስመልክቶ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃልኪ ዳን መፈጸም ያመለክታል (ዘፍ12፥3፤ገላ3፥8:26-29፤ ኢሳ55፥5፤ 56፥6-7 ይመ፤ ከማር11፥17 ጋር ያነጻጽሩ)።

8፥23፤ *ዐሥር፤* በዕብራውያን ዘንድ ከፍተኛ ወይም ፍጹም ቍጥር ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ ነው ዘፍ31፥7 እና ማብ ይመ፤ዘሌ26:26፤ዘኍ14፥22፤1ሳሙ1፥8፤ነህ4፥12 ይመ። *አይሁዳዊ፤* ከምርኮ በኋላ የነበረውን የይሁዳ ሕዝብ ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ሲሆን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው ኤር32፥12 ላይ ነው። *እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር እንዳለ ሰምተናል፤* ትክ ክለኛ የሆነ መንፈሳዊነት ሌሎችን ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ይስ ባል (ዘፍ 26፥28፤30፥27 ይመ፤ እንዲሁም የዘፍ39፥2-6፤1ቆሮ14፥24 ማብ ይመ)።

*9፥1-8፤* እግዚአብሔር እንደ መለኮት ተዋጊ የእስራኤልን ታሪካዊ ጠላቶች ለማጥፋት ከደቡብ ወደ ኢየሩሳሌም መዝመቱን የሚያሳይ ትንቢታዊ መግለጫ ሳይሆን አይቀርም። ታሪክ እንደ ሚያመለክተው እግዚአብሔር ይህን የገለበጠበት መሣሪያ ታላቁ እስክንድር ነው (333 ዓ.ቅ.ክ)።

9፥1፤ *የእግዚአብሔር ቃል፤* በዕብራይስጡ ይህ ሐረግ በብ ሉይ ኪዳን ከዚህ ክፍል ሌላ የተጠቀሰው ሁለት ጊዜ ብቻ ነው (12፥1፤ሚል1፥1)፤ ይህም ዘካርያስ 9-14 እና ትንቢተ ሚልክያስ በተመሳሳይ ዘመን እንደተጻፉ ይጠቍማል (ከመግቢያው “የተጻ ፈበት ዘመን” የሚለውን ይመ)። *በሴድራክ፤* ከሐማት በስተ ሰሜን በኦሮንቶስ ወንዝ ላይ የሚገኝ አካባቢ ነው (ቍ 2 ይመ)። *በደማስ ቆም፤* የአራም ርእስ ከተማ ነች። *ዐይን በእግዚአብሔር ላይ፤* ምናልባት የክፍሉ ሐሳብ የሰዎች፣ በተለይም የእስራኤል ነገዶች ሁሉ ዐይን ትድግናን በመፈለግ ወደ እግዚአብሔር መመለሱን ያሳያል።

9፥2፤ *ደግሞም በአዋሳኟ በሐማት ላይ፤* ፍርድ በሴድራ ክና በደማስቆ ላይ እንደሚደርስ በሐማትም ላይ ይደርሳል። (አሞ6፥2 ይመ)። *በጢሮስና በሲዶና፤* የፊንቄ የአሁኗ ሊባኖስ የጠ ረፍ ከተሞች ናቸው። በእነርሱ ላይ የደረሰው ፍርድ ቍ 3-4 ቀደም ሲል በትንቢት ተነግሮ ነበር (ኢሳ23፤ሕዝ26፥3-14፤28፥20-24፤ አሞ1፥9-10 ይመ)።

9፥3፤ *ምሽግ፤* በዕብራይስጡ ይህ ቃል ሁለት ትርጕም ያለው ሲሆን ፣ አንደኛው ዐለት፣ ሌላው ደግሞ ጢሮስ ማለት ነው። ምሽጉ የጢሮስ ደሴት ዐምባ ነበር (ኢሳ23፥4፤ሕዝ26፥5)። ይህን ዐምባ ታላቁ እስክንድር በ332 ዓ.ቅ.ክ ላይ አፍርሶአታል (ቍ 4)። *ብሩን እንደ ዐፈር ወርቁንም እንደ መንገድ ላይ ትቢያ፤*

5አስቀሎና አይታ ትርዳለች፤
ጋዛ በሥቃይ ትቃትታለች፤
አቃሮናም እንደዚሁ ትሠቃያለች፤ ተስፋዋ
ይመነምናልና::
ጋዛ ንጉሥዋን ታጣለች፤
አስቀሎናም ባድማ ትሆናለች::
6ድብልቅ ሕዝቦች አዛጦንን ይይዛሉ፤
የፍልስጥኤማውያንንም ትምክሕት
እቈርጣለሁ::
7ደሙን ከአፋቸው፣
የተከለከለውንም ምግብ ከመንጋጋቸው
አወጣለሁ::
የተረፉት ለአምላካችን ይሆናሉ፤
በይሁዳም አለቆች ይሆናሉ፤
አቃሮንም እንደ ኢያቡሳዊ ይሆናል::
8እኔ ግን ቤቴን
ከዘራፊ ኀይሎች እጠብቃለሁ፤
ጨቋኝ ከእንግዲህ ሕዝቤን አይወርስም፤
አሁን ነቅቼ እጠብቃለሁና::

## የጽዮን ንጉሥ መምጣት

9አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፤ እጅግ ደስ
ይበልሽ፤
አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፤ እልል በዪ፤
እነሆ፤ ጻደቁና አዳኙ ንጉሥሽ[ከ]፣
ትሑት ሆኖ፣ በአህያ ላይ ተቀምጦ፣
በአህያ ግልገል፣ በውርንጫዪቱ ላይ ሆኖ
ወደ አንቺ ይመጣል::

10ሠረገሎችን ከኤፍሬም፣
የጦር ፈረሶችን ከኢየሩሳሌም እወስዳለሁ፤
የጦርነቱም ቀስት ይሰበራል፤
ሰላምን ለአሕዛብ ያውጃል፤
ግዛቱም ከባሕር እስከ ባሕር፣
ከወንዙም[ኸ] እስከ ምድር[ወ] ዳር ድረስ
ይዘረጋል::
11ለአንቺ ደግሞ፣ ከአንቺ ጋር ከገባሁት የደም
ቃል ኪዳን የተነሣ፣
እስረኞችሽን ውሃ ከሌለበት ጕድጓድ ነጻ
እለቃቸዋለሁ::
12እናንት በተስፋ የምትኖሩ እስረኞች፤ ወደ
ምሽጎቻችሁ ተመለሱ፤
አሁንም ቢሆን ሁለት ዕጥፍ አድርጌ
እንደምመልስላችሁ እናገራለሁ::
13ቀስቴን እንደ ገተርሁ፣ ይሁዳን እገትረዋለሁ፤
ኤፍሬምንም ፍላጻ አደርገዋለሁ፤
ጽዮን ሆይ፤ ልጆችሽን አስነሣለሁ፤
ግሪክ ሆይ፤ በአንቺ ልጆች ላይ ይነሣሉ፤
እንደ ተዋጊ ሰይፍም አደርግሻለሁ::

## እግዚአብሔር ይገለጣል

14*እግዚአብሔር* በእነርሱ ላይ ይገለጣል፤
ፍላጻውም እንደ መብረቅ ይወጣል፤
ጌታ *እግዚአብሔር* መለከት ይነፋል፤
በደቡብም ዐውሎ ነፋስ ውስጥ ይጓዛል፤

9፥5 ኤር47፥5
9፥6 ኢሳ14፥30
9፥7 ኢዮ25፥2፤ ኤር47፥1፤ ኢል3፥4፤ ሶፎ2፥4
9፥8 ኢሳ26፥1፤ 52፥1፤54፥14፤ ኢል3፥17፤ ዘካ14፥21
9፥9 ዘፍ49፥11፤ 1ነገ1፥33:39፤ መዝ24፥7፤149፥2፤ ኢሳ9፥6-7፤43፥3-11፤ 62፥11፤ ኤር23፥5-6፤ ሶፎ3፥14-15፤ ዘካ2፥10፤ ሚክ4፥8፤ ማቴ21፥5፤ ዮሐ12፥15
9፥10 መዝ72፥8፤ ኢሳ2፥4፤ ሆሴ1፥7፤2፥18፤ ሚክ4፥3፤5፥10፤ ዘካ10፥4
9፥11 ዘፀ24፥8፤ ኢሳ10፥4፤ 42፥7፤ ኤር38፥6፤ ማቴ26፥28፤ ሉቃ22፥20
9፥12 ዘዳ21፥17፤ ኢሳ40፥2፤ ኢል3፥16
9፥13 2ሳሙ22፥35፤ ኢሳ49፥2፤ ኤር51፥20፤ ኢል3፥6
9፥14 ዘሌ25፥9፤ መዝ18፥14፤ ኢሳ21፥1፤31፥5፤ 66፥15፤ ዕን3፥11፤ ማቴ24፥31

ከ9 ወይም ንጉሥ ማለት ይሆናል
ኸ10 ኤፍራጥስ ማለት ነው
ወ10 ወይም፣ "*ምድር ዳርቻ*" ማለት ነው::

ከ1ነገ10፥21:27 ጋር ያነጻጽሩ:: ጢሮስ የንግድ ማእከል ነበረች፤ ሀብቷ በምሳሌነት ይጠቀስ ነበር (ኢሳ23፥2-3:8:18፤ሕዝ 26፥12፤ 27፥3-27:33፤28፥45:7:12-14:16-18ይመ)::

9፥5-7፤ የፍልስጥኤም ከተሞች እስክንድር አካባቢውን እየ ወረረ በመምጣቱ ምክንያት፣ እጅግ ተደናግጠው ነበር::

9፥5፤ *ተስፋዋ ይመነምናልና፤* ልክ እንደ አብዛኞቹ ስሜ ናዊ የፍልስጥኤም ከተሞች አቃሮን መከራ በመቀበል የመጀ መሪያዋ ትሆናለች:: የመጣውን የመከራ ማዕበል ጢሮስ ትመክ ትልኛለች ብላ ተስፋ ብታደርግም፣ ጢሮስ ራሷ ተስፋ በሚያስ ቈርጥ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለችው::

9፥6፤ *ድብልቅ፤* የተደባለቀ ብሔር ያለበት ሕዝብ ነው፤ ይህም ከምርኮ በኋላ ያለውን ዘመን ያመለክታል (ነህ13፥23-24):: *ፍልስጥኤማውያን፤* የዘፍ10፥14 ማብ ይመ:: በአንድ ወቅት ከነዓ ንን ሙሉ ለሙሉ ተቈጣጥረው ስለነበረ ምድሪቱ በስማቸው ፓሌ ስቲና ተብላ ተጠራች::

9፥7፤ *ደሙን፤* ለጣዖት የቀረበውን መሥዋዕት ያሳያል:: *የተከለከለውንም ምግብ፤* በሥርዐታቸው መሠረት የረከሰ ምግብ ማለት ነው:: *ኢያቡሳዊ፤* እነዚህ የኢየሩሳሌም የጥንት ነዋሪዎች (የዘፍ10፥16 ማብ ይመ)፤ በይሁዳ ሕዝብ ስለተዋጡ ለምሳሌ:- ኦርና 2ሳሙ24፥16-24፤1ዜና21፥18-26 ይመ፤ ከፍልስጥኤም ቅሬታዎች ጋር ሊሆኑ ይችላሉ::

9፥8፤ *ቤቴን ከዘራፊ ኀይሎች እጠብቃለሁ፤* 2፥5 ይመ:: ትልቁ እስክንድር ቤተ መቅደሱንና የኢየሩሳሌምን ከተማ አድ ኖአል:: *ጨቋኝ፤* በዘ3፥7፤5፥6:10 ላይ እና በሌላም ስፍራ ይኸው የዕብራይስጥ ቃል፣ "ባሪያ ፈንጋይ" ተብሎ ተተርጕሞአል፤ ስለዚ ህም በግብፅ የነበረውን ባርነት ያመለክታል:: *እጠብቃለሁና፤* ዘፀ 3፥7፤መዝ32፥8ይመ::

*9፥9፤* በአዲስ ኪዳን ስለ መሲሑ የተጠቀሰ እና ኢየሱስም በአጀብ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱን የሚያመለክት ነው (ማቴ21፥5፤ ሐሥ-12፥15):: *የጽዮን ልጅ፤* ኢየሩሳሌምንና ነዋሪዎቿን በሰውኛ አገ ላለጽ የሚያሳይ ነው:: *ንጉሥሽ፤* ከዳዊት ዘር የሆነውን ንጉሥ መሲሑን የሚያመለክት ነው:: *ጻድቁና፤* በተለይ በሙሴ ሕግ እንደተገለጠው ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ግብረ ገብና ሥነ ምግባር መጠበቅን ያመለክታል (2ሳሙ 23፥3-4፤ መዝ72፥1-3፤ኢሳ 9፥7፤11፥4-5፤53፥11፤ኤር23፥5-6፤33፥15-16 ይመ):: *ትሑት፤* የተ ዋረደ መንፈስ ያለው ማለት ነው ከኢሳ 53፥23:7፤ማቴ11፥29 ጋር ያነጻጽሩ):: *በአህያ ላይ ተቀምጦ፤* በፈረስ መገልገል ከመ ጀመሩ በፊት፣ ሰላማዊ እንስሳ በመሆኑ፣ የመሳፍንት መገልገያ (መሳ10፥4፤12፥14፤ 2ሳሙ16፥2 ይመ) የነበረው አህያ ከቍ10 ላይ ከተጠቀሱት "የጦር ፈረሶች" ጋር ያነጻጽሩ መምረጡ ተገቢ ነበር፤ ዳዊትና ልጆቹ ይገለገሉበት የነበረው ግን በበቅሎ ነበር 2ሳሙ18፥9፤1ነገ1፥33::

9፥10፤ *ሠረገሎችን...የጦር ፈረሶችን...እወስዳለሁ፤ የጦርነ ቱም ቀስት፤* ተመሳሳይ በሆነ ዘመን የጦር መሣሪያዎች እንደ ሚወገዱ ነቢያት ተንብየዋል ኢሳ2፥4፤9፥5-7፤11፥1-10፤ ሚክ 5፥10-11ይመ:: *ኤፍሬም፤* የቍ13 ማብ ይመ:: *ሰላምን ለአሕ ዛብ፤* የእስክንድር መንግሥት በብዙ የደም መፍሰስ የተመሠረተ ነው፤ የአብርሃም ኪዳን ፍጻሜ ሆኖ የሚመሠረተው የመሲሑ መንግሥት ግን የሰላም መንግሥት ነው:: ከ14፥16፤ ጋር ያነጻ ጽሩ፤ ዘፍ12፥3፤18፥18፤22፥18 ይመ:: *ግዛቱም...እስከ ምድር ዳር ድረስ ይዘረጋል፤* ዓለም ዐቀፋዊ ይሆናል ማለት ነው መዝ 22፥27-28፤72፥8-11፤ ኢሳ45፥22፤52፥10፤66፥18 ይመ::

9፥11፤ *ከአንቺ ጋር ከገባሁት የደም ቃል ኪዳን፤* ምና ልባት ከሙሴ ጋር የተደረገው ቃል ኪዳን ሳይሆን አይቀርም (ዘፀ 24፥38):: *እስረኞችሽን፤* እስካሁን የምርኮ ምድር በሆነችው በባ ቢሎን ያሉትን ሳይሆን አይቀርም:: *ውሃ ከሌለበት ጕድጓድ፤* ከዘፍ37፥24፤ከኤር38፥6 ጋር ያነጻጽሩ::

9፥12፤ *ምሽጎቻችሁ፤* 1) የኢየሩሳሌምንና (ጽዮንን) አካባቢ ዋን ወይም 2)ራሱ እግዚአብሔርን ሊሆን ይችላል ከ2፥5 ጋር ያነ ጻጽሩ:: *በተስፋ፤* ወደፊት ዐርነት በሚያወጣቸው ንጉሥ ማለት ነው ቍ9-10:: *ሁለት ዕጥፍ፤* ፍጹም ወይም ሙሉ የሆነ ተሐድሶ ማለት ነው ከኢሳ61፥7 ጋር ያነጻጽሩ::

*9፥13፤* የ10፥4 ማብ ይመ:: እግዚአብሔር ይሁዳን እንደ ቀስቱ ኤፍሬምን የሰሜኑን መንግሥት ደግሞ እንደ ፍላጻ አድርጎ የሚጠቀም ጦረኛ አድርጎ ራሱን ያቀርባል:: *ጽዮን ሆይ፤ ልጆችሽን፤* መቃብያንን ማለት ነው የዳን11፥34 ማብ ይመ:: *ግሪክ ሆይ፤ በአንቺ ልጆች፤* የእስክንድር ግዛት የጦር ጀነራሎቹ ከሆኑት መካከል የሶርያውን ሴውሉሲድ የሚያመለክት ነው::

9፥14፤ መዝ18፥7-15፤ዕን3፥3-15ይመ:: *መለከት፤* መብረቅን ሊያ መለክት ይችላል (ከዘፀ 19፥16-19 ጋር ያነጻጽሩ):: *በደቡብም፤* የሙሴ ቃል ኪዳን የተሰጠበትንና (ቍ11) እግዚአብሔር የነበረበትን የሲናን ተራራ አካባቢ ያመለክታል (መሳ5፥45፤ መዝ 68፥8፤ ዕን3፥3ይመ)::

15*እግዚአብሔር* ጸባኦትም ይከልላቸዋል፤
ጠላቶቻቸውን ይደመስሳሉ፤
በድንጋይ ወንጭፍም ያሸንፋሉ፤
ይጠጣሉ፤ በወይን ጠጅ እንደ ሰከረ ሰው
ይጮኻሉ፤
የመሠዊያውን ማእዘኖች ለመርጨት፣
እንደ ተዘጋጀ ዕቃ°፣
እነርሱም እንደዚሁ ተሞልተዋል።
16ሕዝቡን የራሱ መንጋ አድርጎ
በዚያ ቀን አምላካቸው *እግዚአብሔር*
ያድናቸዋል።
በአክሊል ላይ እንዳለ ዕንቍ፣
በገዛ ምድሩ ላይ ያብለጨልጫሉ።
17እንዴት ውብና አስደናቂ ይሆናሉ፤
እህል ጎልማሶችን፣
አዲስ የወይን ጠጅም ቈነጃጅትን ያሳምራል።

## እግዚአብሔር ለይሁዳ ይጠነቀቃል

**10** የበልግ ዝናብ እንዲሰጣችሁ *እግዚአብሔርን* ጠይቁ፤
ማዕበሉን ደመና የሚያደርግ *እግዚአብሔር* ነው፤
እርሱ ለሰዎች በቂ ዝናብን፣
ለእያንዳንዱም የምድርን ተክል ይሰጣል።
2ተራፊም አሳሳች ነገር ይናገራል፤
ሟርተኞች የሐሰት ራእይ ያያሉ፤
የውሸት ሕልም ይናገራሉ፤
ከንቱ መጽናናት ይሰጣሉ፤
ስለዚህ ሕዝቡ እንደ በጎች ተቅበዘበዙ፤
እረኛ በማጣትም ተጨነቁ።
3"ቍጣዬ በእረኞች ላይ ነዷል፤
መሪዎችንም እቀጣለሁ፤
*እግዚአብሔር* ጸባኦት፣
ለመንጋው ለይሁዳ ቤት ይጠነቀቃልና፤
በጦርነትም ጊዜ እንደ ክብሩ
ፈረስ ያደርጋቸዋል።
4ከይሁዳ፣ የማእዘን ድንጋይ፣
የድንኳን ካስማ፣
የጦርነት ቀስት፣
ገዥም ሁሉ ይወጣል።
5ጠላትን መንገድ ላይ እንዳለ ጭቃ ይረግጣሉ፤
በአንድነት እንደ ጦር ሰልፈኛ ይሆናሉ፤
እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለሆነ ተዋግተው፣
ፈረሰኞችን ያዋርዳሉ።
6"የይሁዳን ቤት አበረታለሁ፤
የዮሴፍንም ቤት እታደጋለሁ።
ስለምራራላቸው፣
ወደቦታቸው እመልሳቸዋለሁ፤
እነርሱም በእኔ እንዳልተተዉ ሰዎች
ይሆናሉ፤
እኔ አምላካቸው *እግዚአብሔር* ነኝና፣
ጸሎታቸውን እሰማለሁ።
7ኤፍሬማውያን እንደ ኀያላን ሰዎች ይሆናሉ፤
ልባቸውም የወይን ጠጅ እንደ ጠጣ
ሰው ሐሤት ያደርጋል።
ልጆቻቸው ያዩታል፤ ደስተኛም ይሆናሉ፤
ልባቸውም *በእግዚአብሔር* ደስ ይለዋል።
8በፉጨት እጠራቸዋለሁ፤
በአንድነት እሰበስባቸዋለሁ፤
በእርግጥ እቤዣቸዋለሁ፤
እንደ ቀድሞው ይበዛሉ።
9በሕዝቦች መካከል ብበትናቸውም፣
በሩቅ ምድር ሆነው ያስቡኛል፤
እነርሱና ልጆቻቸው ተርፈው፣
በሕይወት ይመለሳሉ።
10ከግብፅ እመልሳቸዋለሁ፤
ከአሦርም እሰበስባቸዋለሁ፤
ወደ ገለዓድና ወደ ሊባኖስ አመጣቸዋለሁ፤

°15 ወይም ጽዋ

9፥15 ዘፀ27፥2፤ ኢሳ31፥5፤ 37፥35፤ዘካ10፥7፤ 12፥8፤14፥3:20፤
9፥16 ኢሳ10፥20፤ ኤር31፥11
10፥1 ዘሌ26፥4፤ 1ነገ18፥36፤ኢዮ 14፥9፤መዝ104፥13፤ 135፥7
10፥2 ዘኍ27፥17፤ ኢሳ40፥19፤44፥25፤ ኤር23፥16፤23፥1፤ ሕዝ21፥21፤ሆሴ 3፥4፤ማቴ9፥36
10፥3 ኢሳ14፥9፤ ኤር25፥34፤ሕዝ 34፥8-10
10፥4 መዝ 118፥22፤ኢሳ22፥23፤ ዘካ9፥10፤ሐሥ4፥11
10፥5 2ሳሙ 22፥43፤አሞ2፥15፤ ሚክ7፥10፤5፥8፤ ሐጌ2፥22፤ ዘካ12፥4
10፥6 መዝ34፥17፤ 102፥13፤ኢሳ14፥1፤ 58፥9፤65፥24፤ ሕዝ30፥24፤ 36፥37፤19፤ዘካ8፥7-8፤13፥9
10፥7 1ሳሙ2፥1፤ ኢሳ60፥5፤ኢል 2፥23፤ዘካ9፥15
10፥8 ኢሳ5፥26፤ ኤር33፥22፤ሕዝ 36፥11
10፥9 ኢሳ44፥21፤ ሕዝ6፥9
10፥10 ኢሳ11፥11፤ 49፥19፤ኤር50፥19፤ ዘካ8፥8

9፥15፤ *በድንጋይ ወንጭፍም፤* የከተማዪቱን ቅጥር በሚጠብቁትና በውስጧ በሚኖሩት ላይ የተወረወረ ነበር። *ለመርጨት እንደ ተዘጋጀ ዕቃ፤* ዘፀ27፥13፤ዘሌ4፥67 ይመ።

9፥16፤ *በዚያ ቀን፤* የ2፥11 ማብ ይመ።

10፥1፤ *እግዚአብሔር...ዝናብን...ተክል ይሰጣል፤* የአየርን ጠባይና ዝናብን የሚቈጣጠር፣ ለምድራቱም ሕይወትንና ልምላሜን የሚሰጥ፣ እግዚአብሔር እንጂ (ኤር14፥22፤አሞ5፥8 ይመ) የከነዓን አምላክ በኣል አይደለም። ስለዚህ የእግዚአብሔር ሕዝብ በአምላኩ መታመንና ወደ እርሱ መጸለይ ይገባዋል። ኢሳ55፥10-12፤ ሆሴ 2፥8፤ 6፥3፤ ኢዮ2፥21-27፤ማቴ5፥45 ይመ።

10፥2፤ *ተራፊም፤* የቤተሰብ አማልክት ናቸው (ዘፍ31፥19 እና ማብ ይመ)። በመሳፍንት ዘመን ለጥንቈላ ሥራ ይጠቀሙበት ነበር (መሳ17፥5፤18፥14-20)። *ሟርተኞች፤* በሐሰተኛ ነቢያት ጐራ የሚፈረጁና እውነተኛ ነቢያትን በሰይጣን መናፍስት የሚቃወሙ ናቸው፤ከኤር23፥30-32፤27፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ። እግዚአብሔር እውነተኛ ነቢያትን በመተው፣ ምሪትን ለማግኘት ወደ ሟርተኞች መሄድን በዘዳ 18፥9-14 በጥብቅ ከልክሎአል (ዘዳ18፥15-22፤ ዮሐ4፥25፤6፥14፤ሐሥ 3፥22:23:26 ይመ)፤ እንዲሁም የዘፍ 30፥27 ማብ ይመ። *ሕዝቡ እንደ በጎች ተቅበዘበዙ፤* ኢሳ53፥6 እና ማብ ይመ። *እረኛ በማጣትም፤* መንፈሳዊ መሪነት የጠፋበት ዘመን ነው (ከማር6፥34 ጋር ያነጻጽሩ)። "እረኛ" የሚለው ቃል፣ መጀመሪያ የቤተ መንግሥት ቋንቋ ነበር፤ ይህም ሰብአዊ ነገሥታትን (2ሳሙ5፥2፤ኢሳ 44፥28፤ኤር23፥2-4) ወይም እግዚአብሔርን እንደ ንጉሥ (መዝ 23፥1፤100፥3፤ሕዝ34፥11-16) ወይም ደግሞ ከዳዊት ዘር የሆነውን መሲሑን ንጉሥ (ሕዝ34፥23-24፤ ዮሐ10፥11-16፤ዕብ 13፥20፤ 1ጴጥ5፥4 የሚያመለክት ነው)።

10፥3፤ *መሪዎችንም እቀጣለሁ፤* ከሕዝ34፥1-10 ጋር ያነጻጽሩ። *እንደ ክብሩ ፈረስ፤* ድል አድራጊ ማለት ነው።

*10፥4፤* በአራማይኩ ትርጒም እንደ ተገለጸው መሲሑን ሳያመለክት አይቀርም። *ለይሁዳ፤* ዘፍ49፥10፤ ኤር30፥21፤ ሚክ5፥2 ይመ። *የማእዘን ድንጋይ ፤* የ3፥9ማብ ይመ፤ በተለይም ኢሳ28፥16፤ኤፌ2፥20 ይመ። *የድንኳን ካስማ፤* ገዥው የሕዝቡ ድጋፍ መሆኑን ያመለክታል፤ የኢሳ22፥23ማብ ይመ፤ ኢሳ22፥24 ይመ። *የጦርነት ቀስት፤* ከመለኮታዊው ጦረኛ አገላለጽ አንዱ ክፍል ነው (ከ9፥13፤መዝ7፥12፤45፥5፤ሰቈ2፥4፤3፥12፤ከዕን3፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

10፥5 *ከእነርሱ፤* የይሁዳ ሕዝብ ማለት ነው (ቍ4)። *እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለሆነ፤* ኢሱ1፥5፤ኤር1፥8:19፤15፥20ይመ። *ያዋርዳሉ፤* መቃብያን ድል በተጐናጸፉ ጊዜ በከፊል የተፈጸመ ነው (በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ማለት ነው)።

10፥6፤ *የይሁዳን...የዮሴፍንም፤* የደቡብና የሰሜኑ መንግሥታት እንደገና አንድ ይሆናሉ (የ8፥13 ማብ ይመ)።

10፥7፤ *ኤፍሬማውያን፤* የ9፥13 ማብ ይመ። *የወይን ጠጅ እንደ ጠጣ ሰው ሐሤት ያደርጋል፤* ከመዝ104፥15 ጋር ያነጻጽሩ።

10፥8፤ *በፉጨት፤* በቀሙ ፊሽካ ማለት ነው፤ ስለ እረኛው የተነገረ ተለዋጭ ዘይቤ ነው (መሳ5፥16ይመ)። *እቤዣቸዋለሁ፤* ዕብራይስጡ ከባርነት ወይም ከምርኮ መታደግ ማለት ነው (ኢሳ 35፥10፤ ሚክ6፥4 ይመ፤ከ1ጴጥ1፥18-19 ጋር ያነጻጽሩ)። *እንደ ቀድሞው ይበዛሉ፤* ዘፀ1፥6-20ይመ።

10፥9፤ *ያስቡኛል፤* "እግዚአብሔር ያስባል ከሚለው የዘካርያስ ስም ትርጒም ጋር ይመሳሰላል፤ ይኸውም እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን ሕዝብና የሰጠውን ተስፋ አይረሳም ማለት ነው። ሕዝቡ አምላኩን ያስባል።

10፥10፤ *ከግብፅ...ከአሦርም፤* ቍ11ይመ። ምናልባት የእስራኤል ሕዝብ የተበተነበትን አገሮች ሁሉ የሚያመለክት ነው፤

በቂ ስፍራም አይገኝላቸውም::
[11]በመከራ ባሕር ውስጥ ያልፋሉ፤
የባሕሩ ማዕበል ጸጥ ይላል፤
የዐባይም ጥልቅ ሁሉ ይደርቃል::
የአሦር ትምክሕት ይዋረዳል፤
የግብፅም በትረ መንግሥት ያበቃል::
[12]*በእግዚአብሔር* አበረታቸዋለሁ፤
በስሙም ይመላለሳሉ፤"
ይላል *እግዚአብሔር* ::

**11** ሊባኖስ ሆይ፤ እሳት ዝግባሽን እንዲበላው፣
ደጆችሽን ክፈቺ!
[2]የጥድ ዛፍ ሆይ፤ ዝግባ ወድቋልና አልቅስ፤
የከበሩትም ዛፎች ጠፍተዋል!
የባሳን ወርካዎች ሆይ፤ አልቅሱ፤
ጥቅጥቅ ያለው ደን ተመንጥሮአልና!
[3]የእረኞችን ዋይታ ስሙ፤
ክብራቸው ተገፎአልና፤
የአንበሶችን ጩኸት ስሙ፤
ጥቅጥቅ ያለው የዮርዳኖስ ደን ወድሟልና!

## ሁለቱ እረኞች

[4]*እግዚአብሔር* አምላኬ እንዲህ ይላል፤
"ለዕርድ የተለዩትን በጎች አሰማራ፤ [5]የገዢ
ቻቸው ያርዷቸዋል፤ ሳይቀጡም ይቀራሉ፤
የሸጧቸውም፣ '*እግዚአብሔር* ይመስገን፤
ባለ ጠጋ ሆኛለሁ!' ይላሉ፤ ጠባቂዎቻቸ
ውም እንኳ አይራሩላቸውም:: [6]ከእንግዲህ
በምድሪቱ ለሚኖረው ሕዝብ አልራራምና"
ይላል *እግዚአብሔር*፤ "ሰውን ሁሉ ለባልን
ጀራውና ለንጉሡ አሳልፌ እሰጣለሁ፤ እነ
ርሱ ምድሪቱን ያስጨንቃሉ፤ እኔም ከእ
ጃቸው አላድናቸውም::"

[7]ስለዚህ ለዕርድ የተለዩትን በጎች፣ በተ
ለይም የተጨቈኑትን አሰማራሁ:: ሁለት
በትሮች ወስጄም፣ አንዱን "ሞገስ" ሌላ
ውንም "አንድነት" ብዬ ጠራኋቸው፤ መን
ጋውንም አሰማራሁ:: [8]በአንድ ወር ውስጥ
ሦስቱን እረኞች አስወገድሁ::

በጎቹ ጠሉኝ፤ እኔም፣ ሰለቸኋቸው፤
[9]"እረኞችሁ አልሆንም፤ የሚሞቱት ይሙቱ ፤
የሚጠፉት ይጥፉ፤ የቀሩትም አንዱ የሌላ
ውን ሥጋ ይብላ" አልኋቸው::

[10]ከዚያም ከአሕዛብ ሁሉ ጋር የገባሁ
ትን ኪዳን ለማፍረስ፣ "ሞገስ" ብዬ የጠራ
ሁትን በትሬን ወስጄ ሰበርሁት:: [11]በዚያም
ቀን ኪዳኑ ፈረሰ፤ ሲመለከቱኝ የነበሩትና
የተጨነቁት በጎችም *የእግዚአብሔር* ቃል
መሆኑን ዐወቁ::

*ˢ5 ወይም ሁሉም ገዦች በአንድነት ማለት ነው፥ እነርሱም*

10፥11 ኢሳ19፥5-7፤51፥10፤ ሕዝ29፥15፤ 30፥13፤ሶፎ2፥13
10፥12 ሕዝ 30፥24፤ሚክ4፥5
11፥1 2ዜና 16፥19፤ሕዝ31፥3፤ ዘካ12፥6
11፥2 ኢሳ2፥13፤ 10፥34፤32፥19
11፥3 ኢሳ5፥29፤ ኤር2፥15፤50፥44፤ ሕዝ19፥9
11፥4 ኤር50፥7፤ ሕዝ34፥2-3
11፥5 ኤር50፥7፤ ሕዝ34፥2-3
11፥6 ኢሳ9፥19-21፤ኤር13፥14፤ ሰቆ2፥21፤5፥8፤ ሚክ5፥8፤7፥2-6፤ ዘካ14፥13
11፥7 ኤር25፥34
11፥8 ሕዝ14፥5
11፥9 ኢ.9፥20፤ ኤር43፥11
11፥10 ቍ7፤መዝ 89፥39፤ኤር14፥21

በተለይም እነዚህ ሁለት አገሮች፣ ባርነትንና ምርኮን ለማሳሰብ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው:: *እሰበስባቸዋለሁ፤* ኢሳ11፥11-16፤ሕዝ 39፥27-29 ይመ:: *ገለዓድና፤* የዘፍ31፥21ማብ ይመ፤ እንዲሁም ማሕ6፥5፤ኤር50፥19፤ሚክ7፥14ይመ:: *ሊባኖስ፤* 2ነገ19፥23፤ ኢሳ 33፥9 እና ማብ፤ 35፥2 እና ማብ፤ ኤር 22፥6 ይመ:: *በቂ ስፍራም አይገኝላቸውም፤* ቍ8፤2፥4 ይመ፤ እንዲሁም የኢሳ49፥1920ማብ ይመ::

10፥11፤ *በመከራ ባሕር ውስጥ ያልፋሉ፤* በቀይ ባሕር መካከል እንዳለፉት ማለት ነው (ዘፀ14፥22 እና ማብ ይመ)::

11፥1-3፤ አንዳንዶች ይህ አጭር ግጥም የሚተረጕሙት በዝግባ፣ በጥድና በዋርካ (ቍ1-2) የተመሰለውን የአሕዛብ ኀይልና እብሪት (ም10) የሚያፈርስ መሆኑን ለማመልከት፣ ለቅሰቀሳ እን ደሚዘመር እንጕርጕሮ ነው:: ነገሥታቶቻቸው ደግሞ በእረኞችና በአንበሶች ተመስለዋል (ቍ3):: ይህን ክፍል በዚህ መልኩ የም ንረዳው ከሆነ ከቍ1-3 ያለው ከላይ ለተጠቀሰው መደምደሚያ ነው:: ምንም እንኳ አንዳንዶች በክፍሉ ውስጥ የተጠቀሱ ዘይ ቤያዊ አነጋገር መሆናቸው ባይካዱም፣ እያንዳንዱን ቃል በቃል በመተርጐም፣ሶርያና ፍልስጥኤም መልካም እረኛ የሆነውን መሲሕ በመቃወማቸው ምክንያት ጥፋት ይደርስባቸዋል ይላሉ (ቍ4፥1-4):: ስለዚህ ቍ1-3 ያለውን በዚህ መልኩ የምንረዳው ከሆነ ለሚቀጥ ለው ክፍል መግቢያ ይሆናል ማለት ነው:: ክፍሉ ስለ ሊ ባኖስ፣ ስለባሳንና ስለ ዮርዳኖስ የሚቀርበው መልክዐ ምድራዊ ገለጻ ከሁለተኛው ትንታኔ ጋር የሚሄድ ይመስላል:: በመጀመሪያ ሮማው ያን ይህን አካባቢ በተቈጣጠሩበት ጊዜና በ70 ዓ.ም ላይ ደግሞ ኢየሩ ሳሌምን እንዲሁም በ73 ዓ.ም ማሳዳን በደመሰሱበት ወቅት ይህ ትንቢት በከፊል ተፈጽሞአል:: እንግዲህ ከላይ ያለውን ሐሳብ በዚህ መልኩ የምንረዳው ከሆነ፣ ክፍሉ ከም10 ጋር በአያሌው የሚነጻጸርና እስራኤል በቃል ኪዳኒቱ ምድር ፍጹም የሆነ ዐርነት እንዲሁም ተሐድሶ እንደምታገኝ የሚያመለክት ትንቢት ነው:: ስለዚህ ከቍ1-3 ያለው ክፍል በምድሪቱ ላይ ጥፋት እንደ ሚመጣ፣ከቍ46 ባለው ክፍል ደግሞ በሕዝቡና በምድሪቱ ላይ ፍርድና ጥፋት እንደሚከተል ያመለክታል::

11፥1፤ *ሊባኖስ፤* 10፥10 እና ማብ ይመ::

11፥2፤ *የባሳን፤* የኢሳ2፥13ማብ ይመ:: እስራኤላውያን ከነዓንን ድል ባደረጉ ጊዜ ይህን ቦታ ከአሞራውያን ንጉሥ ከዐግ ወስደው ነበር (ዘኍ21፥33-35):: ይህ ቦታ ለምናሴ ነገድ እኩ ሌታ የተሰጠ ነበር (ኢያ13፥29-30፤17፥5):: *ጥቅጥቅ ያለው ደን፤* የሊባኖ ስን ማለት ነው::

11፥3፤ ክፍሉ ዘይቤያዊ አነጋገር ከሆነ እረኞችና አንበሶች የተባሉት የአይሁድን መሪዎችና ገዥዎች ያመለክታሉ (ቍ5፤ 10፥3 ይመ፤ ከኤር25፥34-36 ጋር ያነጻጽሩ:: *ጥቅጥቅ ያለው የዮርዳኖስ ደን፤* የአንበሶች ጕሬ ያለበት ስፍራ ለማለት ነው::

*11፥4-14፤* በቍ1-3 ላይ በእስራኤል ላይ የተፈረደበት ምክ ንያት ሕዝቡ እረኛና ንጉሡ የሆነውን መሲሕ ስላልተቀበለ መሆኑ በዚህ ክፍል ተገልጾአል:: ይህም አገልጋዩ፣ "በአገልጋዩ መዝሙሮች" (የኢሳ42፥1-4ማብ ይመ) እንደተናቀው፣ በዚህም ክፍል መልካሙ እረኛ ተንቆአል:: በሁለቱም ክፍሎች ውስጥ መሲሑ የሆነው ንጉሥ ተጠቅሶአል::

11፥4፤ *ይላል፤* የሚናገረው ለዘካርያስ ነው:: *በጎች፤* እስራ ኤልን ያመለክታል::

11፥5፤ *የገዢቻው፤* በጎቹ የአይሁድ ሕዝብ እንደ ባሪያ በውጭ ሰዎች ተገዝተዋል:: ይህም በ70 ዓመተ ምሕረትና ከዚያም በኋላ በነበሩት ጊዜያት የተፈጸመ ነው:: *የሸጧቸውም፤* "የራሳቸው እረኞች" ናቸው፤ ይኸውም ገዦችን ወይም መሪዎች ማለት ነው::

11፥6፤ *በምድሪቱ፤* ፓሌስቲናን ማለት ነው:: *ለንጉሡ፤* ምናልባትም የሮማውን ዐፄ ንጉሠ ነገሥት ሳይሆን አይቀርም (ከዮሐ19፥15 ጋር ያነጻጽሩ):: *እነርሱ፤* በትንቢት ውስጥ ሮማው ያንን ሁሉ ይጨምራል::

11፥7፤ *አሰማራሁ፤* በዚህ ስፍራ ዘካርያስ ሊመጣ ላለው እረኛና ንጉሥ ለሆነው መሲሕ ምሳሌ ሆኖ ቀርቦአል:: *አንዱን "ሞገስ"...ብዬ ጠራኋቸው፤* እግዚአብሔር መንጋውን እንደ ሚወድ የሚያረጋግጥ ነው:: *"አንድነት"፤* ሕዝ37፥15-28 ይመ:: እንዲህ ዐይ ነቱ አንድነት ከመልካሙ እረኛ በጎ አመራር የሚገኝ ነው::

11፥8፤ *ሦስቱን እረኞች አስወገድሁ፤* ሦስቱ እረኞች እነማን እንደ ሆኑ ባይገለጽም፣ መልካሙ እረኛ ለስፍራው ተገቢ ያል ሆኑትን መሪዎች እንደሚያስወግዳቸው ያሳያል:: *እኔም ሰለቸኋቸው፤* ከኢሳ 1፥13-14 ጋር ያነጻጽሩ::

11፥9፤ *የሚሞቱት ይሙቱ፤* መልካሙ እረኛ ለመንጋው የሚያደርገውን ጥበቃ እንደሚያቋርጥ ያሳያል:: *አንዱ የሌላውን ሥጋ ይብላ፤* የሴፍ ወልደኮሪዮን የተባለው አይሁዳዊ የታሪክ ጸሓፊ በ70 ዓ.ም ሮማውያን ኢየሩሳሌምን በከበቡበት ጊዜ ይህ ትንቢት እንደተፈጸመ ገልጾአል (እንዲሁም ከሰቆ4፥10 ጋር ያነጻጽሩ)::

11፥10፤ *ኪዳን፤* እረኛው ሕዝቡን ከአሕዛብ መንግሥታት ጥቃት ለመጠበቅ የገባው ኪዳን ሳይሆን አይቀርም፤ (ከሕዝ 34፥25፤ሆሴ2፥18ጋር ያነጻጽሩ):: አሁን ግን እንደ ሮማውያን ያሉ የአሕዛብ መንግሥታት ኢየሩሳሌምን እንዲወሩ ተፈቅዶላቸዋል::

11፥11፤ **የተጨነቁት በጎችም፤** የእግዚአብሔርን ሥልጣናዊ ቃል ያስተዋሉ ጥቂት ታማኞችን ሊያመለክት ይችላል (በቍ7 ላይ ይመ፤ የዕብራይስጡ ቃል፣ "የተጨነቁትን (በጎች)" ለማመልከት

12እኔም፣ “የሚበጅ መስሎ ከታያችሁ ዋጋ
ዬን ክፈሉኝ፤ አይሆንም ካላችሁም ተውት”
አልኋቸው፤ ስለዚህ ሠላሳ ብር ከፈሉኝ::
13*እግዚአብሔርም* ሊከፍሉኝ የተስማሙ
በትን ጥሩ ዋጋ “በግምጃ ቤቱ ውስጥ አኑ
ረው” አለኝ፤ እኔም ሠላሳውን ብር ወስጄ
*በእግዚአብሔር* ቤት ባለው ግምጃ ቤት
አስቀመጥሁት:: 14ከዚያም የእስራኤልንና
የይሁዳን ወንድማማችነት በማፍረስ፣ “አን
ድነት” ብዬ የጠራሁትን ሁለተኛውን በት
ሬን ሰበርሁት::
15*እግዚአብሔርም* እንዲህ አለኝ፤ “እንደ
ገና የሰነፍ እረኛ ዕቃ ውሰድ፤ 16እነሆ፤ በም
ድሪቱ ላይ እረኛ አስነሣለሁ፤ እርሱም የጠ
ፋውን አያስብም፤ የባዘነውን አይፈልግም፤
የተሰበረውን አይጠግንም፤ የዳነውንም አይ
ቀልብም፤ ነገር ግን የሰባውን ሥጋ ይበላል፤
ሰኰናውንም ሳይቀር ይቀለጣጥማል::

17 “*መንጋውን ለሚተው፣*
*ለማይረባ እረኛ ወዮለት!*
ሰይፍ ክንዱንና ቀኝ ዐይኑን ትውጋው፤
ክንዱ ፈጽማ ትስለል፤
ቀኝ ዐይኑም ጨርሳ ትታወር::”

## የኢየሩሳሌም ጠላቶች እንደሚደመሰሱ የተነገረ ንግር

12 ስለ እስራኤል የተነገረው *የእግዚአ
ብሔር* ቃል ይህ ነው፤ ሰማያትን የዘ
ረጋ፣ ምድርን የመሠረተ የሰውንም መን
ፈስ በውስጡ የሠራ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ 2“ኢየሩሳሌምን በዙሪያዋ ላሉት ሕዝ
ቦች ሁሉ የሚያንገደግድ ጽዋ አደርጋታ
ለሁ፤ ይሁዳም እንደ ኢየሩሳሌም ሁሉ ትከ
በባለች:: 3የምድር አሕዛብ ሁሉ በእርሷ
ላይ በሚሰበሰቡበት በዚያ ቀን፣ ኢየሩሳ
ሌምን ለአሕዛብ ሁሉ የማይነቃነቅ ዐለት
አደርጋታለሁ፤ ለማንቃነቅ የሚሞክሩ ሁሉ
ራሳቸውን ይጐዳሉ:: 4በዚያን ቀን እያንዳን
ዱን ፈረስ በድንጋጤ፣ የተቀመጡባቸው
ንም ሰዎች በእብደት እመታለሁ” ይላል
*እግዚአብሔር*:: “የይሁዳን ቤት በዐይኔ እጠ
ብቃለሁ፤ ነገር ግን የአሕዛብን ፈረሶች ሁሉ
አሳውራለሁ:: 5የይሁዳ መሪዎች በልባቸው፣
‘የኢየሩሳሌም ሕዝቦች ብርቱ ናቸው፤ አምላ
ካቸው *እግዚአብሔር* ጸባኦት ነውና’ ይላሉ::
6“በዚያ ቀን የይሁዳን መሪዎች በዕን
ጨት ክምር ውስጥ እንዳለ የእሳት ምድጃ፣
በነዶም መካከል እንዳለ የፋና ነበልባል አደ
ርጋቸዋለሁ፤ በግራና በቀኝ ዙሪያውን ያሉ
ትን ሕዝቦች ይበላሉ፤ ኢየሩሳሌም ግን ከስ
ፍራዋ ንቅንቅ አትልም::
7“የዳዊት ቤትና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች
ክብር ከይሁዳ ክብር እንዳይበልጥ እግዚአ
ብሔር በመጀመሪያ የይሁዳን መኖሪያ
ዎች ያድናል:: 8ከመካከላቸው እጅግ ደካማ
የሆነው እንደ ዳዊት፣ የዳዊት ቤትም ፊት
ፊታቸው እንደሚሄድ እንደ *እግዚአብሔር*
መልአክ፣ እንደ አምላክ ይሆንላቸው ዘንድ
በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን *እግዚአብሔር*
ይከልላቸዋል:: 9በዚያ ቀን ኢየሩሳሌምን
በወጓት አሕዛብ ሁሉ ላይ እወጣለሁ::

11፥12 ዘፍ23፥16፤ ማቴ26፥15
11፥13 ዘፀ21፥32፤ ማቴ27፥9-10፤ ሐሥ1፥18-19
11፥17 ኢሳ13፥1፤ ኤር23፥1፤ሕዝ 30፥21-22
12፥1 ዘፍ1፥8፤ መዝ104፥2፤102፥25፤ ኢሳ57፥16፤ኤር 51፥15፤ ዕብ1፥10
12፥2 መዝ60፥3፤ 75፥8፤ኢሳ51፥23፤ ዘካ14፥14
12፥3 ኢሳ29፥8፤ 28፥16፤66፥18፤ ዳን2፥34-35፤ ዘካ 14፥2፤
12፥4 መዝ76፥6፤ ዘካ14፥2፤
12፥5 ሕዝ30፥24
12፥6 ኢሳ10፥17-18፤ አብ1፥18፤ ዘካ11፥1፤14፥10
12፥7 ኤር30፥18፤ አሞ9፥11
12፥8 መዝ82፥6፤ 91፥4፤ኢል3፥10፤ 3፥16፤ሚክ7፥8፤ ዘካ9፥15
12፥9 ኢሳ29፥7፤ ዘካ1፥21፤14፥2-3፤

ጥቅም ላይ ውሎአል):: በኢየሩሳሌምና በቤተመቅደሱ ላይ በ 70 ዓመተ ምሕረት የደረሰውን ፍርድ ዐይነት እንደሚያስከትል በቅዱስ ቃሉ የተረጋገጠ ነው::

11፥12፤ *ዋጋዬን ክፈሉኝ፤* ግንኙነታቸው እንደሚቋረጥ የሚያመለክት ነው:: *ሠላሳ ብር፤* በጥንት ጊዜ በእስራኤላውያን ዘንድ ለአንድ ባሪያ መግዣ የሚከፈል ዋጋ ነው የዘፀ 21፥32 ማብ ይመ፤ ዋጋው ምን ያህል አነስተኛ እንደሆነም ያመለክታል::

11፥13፤ *ጥሩ ዋጋ፤* ምጸታዊ ንግግር ነው:: *በእግዚአ ብሔር ቤት ባለው ግምጃ ቤት አስቀመጥሁት፤* ቍ12:13 በተመለከተ ከአዲስ ኪዳን ማቴ26፥14-15፤27፥3-10፤ እንዲሁም የማቴ27፥9 ማብ ይመ::

11፥14፤ *“አንድነት” ብዬ የጠራሁትን ሁለተኛውን በትሬን ሰበርሁት፤* የሰሜኑንና የደቡብን መንግሥት አንድ ለማድረግ የተደረገው ኪዳን መፍረሱን ያመለክታል:: ሕዝቡ ለሁለት መከፈሉና አንዱ በሌላው ላይ ጠላት መሆኑ በአይሁድ ታሪክ አንዱ መለያና፣ ከሮማውያንም ጋር በነበረባቸውም ጦርነት ዕንቅፋት የፈጠረ ነገር ነበር (ከሐሥ11፥48 ጋር ያነጻጽሩ)::

11፥15፤ *እንደ ገና፤* ቍ7 ይመ:: *የሰነፍ እረኛ፤* እግዚአብሔር የመረጠው እረኛ ከስፍራው ሲወገድ፣ ሰነፍና የማይረባ እረኛ (ቍ17) በእርሱ ፈንታ ይተካል:: ራስ ወዳድ ፣ሥሥታምና ብልሹ መሪ ተነሥቶ መንጋውን ያሠቃያል::

11፥16፤ *የባዘነውን አይፈልግም፤* ከዘፍ33፥13፤ኢሳ 40፥11 ጋር ያነጻጽሩ:: *ሰኰናውንም ይቀለጣጥማል፤* ከስግብግብነታቸው የተነሣ የማይበላውን እንኳ ይበላሉ ማለት ነው::

11፥17፤ *መንጋውን ለሚተው፤* በዮሐ10፥11-16 ላይ ከተገለጸው መልካሙ እረኛ ጋር ያነጻጽሩ:: *እረኛ፤* የ ቍ15ማብ ይመ:: ይህ ዐይነት አስመሳይ እረኛ አይሁዳውያንን በሮማውያን ላይ ባሳመፀው በ132-135 ዓ.ም በሲሞን ባር ኮሺባ ወይም በኮክሐባ በከፊል ተፈጻሚነት አግኝቶአል፤ ይህም ሰው አኪባ በሚባል ራቢ መምህር መሲሑ ነው ተብሎም ነበር:: ይህ ትንቢት ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚነት የሚያገኘው ግን የክርስቶስ ተቃዋሚው ሲመጣ ነው (ከሕዝ34፥2-4፤ ዳን11፥36-39፤ ከዮሐ 5፥43፤ 2ተሰ2፥3-10፤ከራእ13፥1-8 ጋር ያነጻጽሩ):: *ክንዱ ፈጽማ ትስለል፤* ኀይሉ ፈጽሞ ይድከም ማለት ነው:: *ቀኝ ዐይኑም ጨርሳ ትታወር፤* ዕውቀቱ ሙሉ ለሙሉ ከንቱ ይሁን ማለት ነው:: ይህ ከሆነ መሪው ለመዋጋት ጕልበት አይኖረውም::

12፥1-14፥21፤ በመጽሐፉ ሁለተኛ ክፍል ላይ የሚገኘው ይህ ሁለተኛው ንግር፣ በሁለት አርእስተ ጕዳዮች ላይ ያውጠነጥናል፤ እነርሱም መከበብና መሲሑ የእስራኤልን ጠላቶች ደምስሶ የራሱን መንግሥት ማቋቋሙን ነው::

12፥1፤ *እስራኤል፤* የሰሜኑን መንግሥት ብቻ ሳይሆን፣ የደቡብንም መንግሥት የሚጨምር ነው:: ትኵረት የተደረገውም በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ነው:: *የተነገረው፤* የ9፥1ማብ ይመ:: *የዘረጋ፣...የመሠረተ...የሠራ እግዚአብሔር፤* የእግዚአብሔርን የፈጣሪነት ሥራ፣ የተናገረውን ሁሉ መፈጸም የሚችል አምላክ መሆኑንና የቃሉን ሥልጣን ያሳያል::

12፥2፤ *የሚያንገደግድ ጽዋ፤* የኢሳ51፥17 ማብ ይመ::

12፥3፤ *አሕዛብ ሁሉ በእርሷ ላይ በሚሰበሰቡበት፤* 4፥2:12፤ ኢዮ3፥9-16ይመ፤ ከራእ16፥16-21ጋር ያነጻጽሩ:: *በዚያ ቀን፤* የ2፥11 ማብ ይመ:: ይህ ሐረግ በአብዛኛው በም 12-14 ባለው ክፍል ይገኛል (12፥4:6:89:11፤13፥12:4፤14፥4:6:8:9:13፡ 20:21)::

*12፥4፤* እስራኤላውያን ለቃል ኪዳኑ ባይታዘዙ በዘዳ28፥28 ላይ ከሚደርስባቸው ርግማኖች መካከል እነዚህ ይገኙበታል፤ አሁን ግን ርግማኑ በእስራኤል ጠላቶች ላይ ሆነ:: *በዐይኔ እጠብቃለሁ፣* መዝ32፥8፤33፥18 ይመ::

*12፥6፤* እሳት ዕንጨትና የእህልን ገለባ እንደሚበላ የይሁዳም አስተዋይ መሪዎች (ቍ5) ጠላቶቻቸውን ድጋ ዐመድ ያደረጓቸዋል (ከመሳ15፥3-5 ጋር ያነጻጽሩ፤ የኢሳ1፥31 ማብ ይመ)::

12፥8፤ *እንደ ዳዊት ፤* እንደ ብርቱ ጦረኛ ለማለት ነው:: *እንደ አምላክ፤* ከዘፀ 4፥16፤7፥1 ጋር ያነጻጽሩ:: *እንደ እግዚአብሔር መልአክ፤* ዘፍ 48፥16 እና ማብ፤ ዘፀ14፥19፤23፥20፤ 32፥34፤33፥2:14:15:22፤ሆሴ12፥3-4፤ እንዲሁም ዘፍ16፥7 እና ማብ ይመ::

## ስለ ወጉት የተደረገ ሐዘን

[10]"በዳዊት ቤትና በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች
ላይ የርኅራኄና የልመና መንፈስ አፈሳለሁ፤
ወደ ወጉኝ ወደ[a] እኔም ይመለከታሉ፤ እነ
ርሱም ለአንድያ ልጅ እንደሚለቀስ ያለቅ
ሱለታል፤ ለበኵር ልጅ ምርር ተብሎ እን
ደሚለቀስም አምርረው ያለቅሱለታል።"
[11]በዚያ ቀን በመጊዶን ሜዳ ለሐዳድሪሞን
እንደተለቀሰ ሁሉ በኢየሩሳሌም የሚለቀስ
ውም እንደዚሁ ታላቅ ልቅሶ ይሆናል።
[12]ምድሪቱ ታለቅሳለች፤ የየነገዱ ወንዶች
ለየራሳቸው ያለቅሳሉ፤ ሚስቶቻቸውም ለየራ
ሳቸው ያለቅሳሉ፤ በዚህም ዐይነት የዳዊት ቤት
ነገድ ወንዶች ከነሚስቶቻቸው የናታን ቤት
ነገድ ወንዶች ከነሚስቶቻቸው፣ [13]የሌዊ ቤት
ነገድ ወንዶች ከነሚስቶቻቸው፣ የሰሜኢ ቤት
ነገድ ወንዶች ከነሚስቶቻቸው፣ [14]የቀሩትም
ነገዶች ወንዶች ሁሉ ከነሚስቶቻቸው ያለ
ቅሳሉ።

## ከኀጢአት መንጻት

13 "በዚያ ቀን የዳዊትን ቤትና የኢ
የሩሳሌምን ነዋሪዎች ከኀጢአትና
ከርኵሰት የሚያነጻ ምንጭ ይከፈታል።
[2]"በዚያ ቀን የጣዖታትን ስም ከምድሪቱ
አጠፋለሁ፤ ከእንግዲህም አይታሰቡም" ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት። "ነቢያትንና ርኵስ
መንፈስን ከምድሪቱ አስወግዳለሁ። [3]ማንም
ትንቢት ቢናገር ወላጅ አባትና እናቱ፣
'በእግዚአብሔር ስም ሐሰት ተናግረሃልና
ሞት ይገባሃል' ይሉታል፤ ትንቢት ሲናገርም
የገዛ ወላጆቹ ይወጉታል።
[4]"በዚያን ቀን እያንዳንዱ ነቢይ ስለሚ
ናገረው የትንቢት ራእይ ያፍራል፤ ለማታ
ለልም የነቢያትን ጠጕራም ልብስ አይለብ
ስም። [5]እርሱም፣ 'እኔ ገበሬ እንጂ ነቢይ
አይደለሁም፤ ከልጅነቴ[b] ጀምሮ ኑሮዬ የተ
መሠረተውም በዕርሻ ላይ ነው' ይላል።
[6]አንድ ሰው፣ 'ይህ በሰውነትህ[c] ላይ ያለው
ቍስል ምንድን ነው?' ብሎ ቢጠይቀው፣
'በባልንጀሮቼ ቤት ሳለሁ የቈሰልሁት ነው'
ይላል።

## እረኛው ተመታ፤ በጎቹ ተበተኑ

[7]እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
"ሰይፍ ሆይ፤ በእረኛዬ፣
በቅርብ ወዳጄ ላይ ንቃ!
እረኛውን ምታ፤
በጎቹ ይበተናሉ፤
እኔም ክንዴን ወደ ታናናሾቹ እዘረጋለሁ።
[8]እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ "የምድር ሁሉ፣
ሁለት ሦስተኛው ተመትቶ ይጠፋል፤
አንድ ሦስተኛው ግን በውስጡ ይቀራል፤
[9]ይህን አንድ ሦስተኛውን ክፍል ወደ እሳት
አመጣለሁ፤
እንደ ብር አነጥራቸዋለሁ፤
እንደ ወርቅም እፈትናቸዋለሁ፤

12፥10 ዘኍ21፥16፤ መሳ11፥34፤መዝ22፥16፤ኢሳ44፥3፤ኤር31፥19፤ሕዝ37፥9፤39፥29፤ኢዩ2፥28-29፤ዮሐ19፥34፡37
12፥11 2ነገ23፥29፤ ኤር50፥4
12፥12 ማቴ24፥30፤ ራእ1፥7
12፥14 ዘካ7፥3
13፥1 ዘሌ16፥30፤ መዝ51፥2፤ኤር17፥13
13፥2 1ነገ22፥22፤ ኤር23፥14-15፤ 43፥12፤ሕዝ6፥6፤ 36፥25፤ሆሴ2፥17፤ ሚክ5፥13
13፥3 ዘዳ13፥6-11፤ 18፥20፤ነህ6፥14፤ ኤር23፥34፤28፥16፤ ሕዝ14፥9
13፥4 1ነገ18፥7፤ ኢሳ20፥2፤ኤር6፥15፤ሕዝ12፥24፤ ማቴ3፥4
13፥5 አሞ7፥14
13፥7 ማቴ26፥31፤ ማር14፥27 2ሳሙ17፥2፤
13፥8 ሕዝ5፥2-4 ፡12፤ዘካ14፥2
13፥9 ዘሌ26፥12፤ ኢዮ6፥29፤መዝ12፥6፤50፥15፤ 86፥7፤105፥1፤ ኢሳ4፥4፤30፥19፤ 33፥14፤44፥5፤ ኤር6፥27፤29፥12፤ 30፥22፤ሕዝ20፥38፤ ዳን11፥35፤ዘካ10፥6፤ሚል3፥2፤1ጴጥ1፥6-7

[a]10 ወይም እኔን
[b]5 ወይም እራሼ፤ በመጣትነቴ የተሸጥሁ ሰው
[c]6 በእጆችህ መካል ይሉ ቍስሎች የሚሉ አሉ።

12፥10፤ መንፈስ፤ ኢሳ32፥15 እና ማብ፤ 44፥3፤ 59፥20-21፤ ኤር 31፥31፡33፤ሕዝ 36፥26-27፤39፥29፤ኢዮ2፥28-29 ይመ። ወደ…ይመለከታሉ፤ መሲሑን በእምነት በመመልከት ላይ አጽንዖት ያደርጋል። ከዘኍ 21፥9፤ ከኢሳ45፥22፤ ከዮሐ3፥14-15 ጋር ያነጻጽሩ። ወደ ወጉኝ ከመዝ22፥16፤ ኢሳ53፥5፤ከዮሐ 19፥34 ጋር ያነጻጽሩ፤ ይህም በዮሐ19፥37 ላይ በከፊል ተፈጽሞአል። ለአንድያ ልጅ እንደሚለቀስ፤ ከኤር 6፥26 ጋር ያነጻጽሩ። ለበኵር ልጅ ምርር ተብሎ እንደሚለቀስም፤ ከዘፀ 11፥5-6 ጋር ያነጻጽሩ።

12፥11፤ ለሐዳድሪሞን፤ ይህ ስም፦ 1) በመጊዶ አጠገብ ለሚገኝ ቦታ የተሰጠና ሕዝቡ ንጉሥ ኢዮስያስ በሞቱ ጊዜ ያለ ቀሱበት ቦታ ነው (2ዜና35፥20-27፤22 ስለ መጊዶ ሜዳ እና ቍ 24-25 ስለ ልቅሶው) ወይም 2) ባቢሎናውያን "ኑጉድጓዱ ሐዳድ" ብለው ለሚጠሩት ለሲሚውያን የማዕበል አምላክ (2ነገ5፥18 ይመ) የተሰጠ ነው። በሕዝ8፥14 ለባቢሎናውያን አምላክ እን ዲት እንደሚለቀስ ይመ።

12፥12፤ ናታን፤ የዳዊት ልጅ ነው (2ሳሙ5፥14 ይመ፤ ከሉቃ 3፥31 ጋር ያነጻጽሩ)።

12፥13፤ ሰሜኢ፤ የሌዊ ልጅ የጌድሶን ልጅ ነው (ዘኍ 3፥17-18፡21)። በዚያ ጊዜ ንስሓና ልቅሶ በአገርና በሃይማኖት መሪዎች ይካሄድ ነበር።

13፥1፤ ከኀጢአትና…የሚያነጻ፤ 3፥4-9 ይመ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙ ተስፋዎች መካከል አንዱ ነው (ኤር 31፥34፤ ሕዝ 36፥25)።

13፥2፤ የጣዖታትን ስም፤ ጣዖታቱ የሚያሳድሩት ተጽዕኖና ዝና እንዲሁም የሕልውናቸው መሠረት ማለት ነው። ነቢያትንና፤ ከምርኮ በኋላም በነበሩት ጊዜያት ሐሰተኛ ትንቢቶች ጭምር ፈጥረው ነበር (ነህ6፥12-14)፤ ይኸውም ችግር ወደፊትም ይቀጥላል (ማቴ24፥4-5፡11፡23-24፤ 2ተሰ2፥2-4 ይመ)።

13፥3፤ ሐሰት፤ የውሸት ትንቢቶች ለማለት ነው። ወላጅ ሞት ይገባሃል፤ ዘዳ13፥69 ላይ ባለው ትእዛዝ መሠረት ማለት ነው። መሲሑን ለመውጋት የነበራቸው ፍላጎት፣ አሁን ወደ ሐሰ ተኛ ነቢያት ያነጣጥራል።

13፥4-6፤ ከእንዲህ ዐይነቱ ጠንካራ ርምጃ የተነሣ ሐሰተኛ ነቢይ ራሱን ለማሳወቅ ብዙ አይደፍርም፤ቢጠየቅም እንኳ መልስ ለመስጠት አይፈልግም። እውነተኛ ማንነቱን ለመሸፈን እንኤልያስ የለበሱትን የነቢያት ልብስ (ቍ4) አይለብስም (2ነገ1፥8 ይመ)፤ እንዲሁም ማቴ3፥4 ከሞት ቅጣትም ለመሸሽ (ቍ3) ነቢይነቱን በመካድ ከልጅነቱ ጀምሮ ገበሬ እንደነበር ይናገራል (ቍ5)። ተጠራጣሪ ሰው በሰውነቱ ላይ ያለውን ቍስል አይቶ ስለዚሁ ጕዳይ ቢጠይቀው ቍ6 ከባልንጀሮቹ ጋር በተጣላ ጊዜ ወይም ወላጆቹ ሲቀጡት የደረሰበት ጕዳት እንደሆነ ይናገራል። ጠ ያቂው ግን ሐሰተኛ ነቢዩ የጣዖት አምልኮውን ሥርዐት ሲፈ ጽም፣ መንፈሱን ለማነሣሣት ሲል ራሱን ያቈሰለ መሆኑን በግልጽ ይረዳል (1ነገ18፥28 ይመ፤ እንዲሁም ከዘሌ19፥28፤21፥5 እና ማብ፤ ዘዳ14፥1፤ኤር16፥6፤41፥5፤48፥37 ጋር ያነጻጽሩ)።

13፥5፤ ከልጅነቱ…በዕርሻ፤ አማራጭ ትርጕሙ ትክክል ከሆነ፣ ገና ልጅ ሳለ በባርነት ተሸጦአል ማለት ነው።

13፥6፤ አንዳንዶች ይህ ጥቅስ ስለ መሲሑ የሚናገር ነው ይላሉ። ነገር ግን ከዐውደ ምንባቡ ጋር የሚስማማው ከላይ የተ ሰጠው ማብ ነው (ቍ5)።

13፥7፤ በእረኛዬ፤ መልካም እረኛ የሆነውን መሲሕ የሚያ መለክት ነው (በ11፥4-14ላይ ያለውን እውነተኛ እረኛ በ11፥15-17 ላይ ካለው ሰነፍ እረኛ ጋር ያነጻጽሩ)። እረኛውን ምታ፤ በ11፥17 ላይ መመታት የነበረበት የማይረባው እረኛ ነው፤ በዚህ ስፍራ ግን መልካሙን እረኛ ያመለክታል (ከ2፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። በጎቹ ይበተናሉ፤ ቃል ኪዳኑን ካለመታዘዝ የተነሣ የሚደርስ ርግ ማን ነው ዘዳ28፥64፤29፥24-25። ኢየሱስ ዕልፍ ከመስጠቱ በፊት ይህን ክፍል ተጠቅሶ ነበር (ማቴ26፥31፤ማር14፥27) የሐዋርያትን መበተን አስመልክቶ ተናግሮአል (ማቴ26፥56፤ማር14፥49-50)፤ በሌላ በኩል ደግሞ በ70 ዓመተ ምሕረትና ከዚያም በኋላ በተከታታይ በነበሩት ዓመታት የአይሁድን መበተን የሚያመለክት ነው።

13፥8-9፤ ይህ ክፍል የእስራኤል እየነጠረች የምትሄድበትን ሂደት የሚያሳይ ነው (የኢሳ48፥10ማብ ይመ)።

13፥8፤ አንድ ሦስተኛው፤ በፍርድ ጊዜ እግዚአብሔር ምሕረቱን የሚገልጥባቸው ቅሬታዎች እንዳሉ የሚያመለክት ነው።

እነርሱ ስሜን ይጠራሉ፤
እኔም እመልስላቸዋለሁ፤
እኔም፣ 'ሕዝቤ ናቸው' እላለሁ፤
እነርሱም፣ '*እግዚአብሔር* አምላካችን ነው'
ይላሉ።"

## እግዚአብሔር ይመጣል፤ ይነግሣልም

**14** እነሆ፤ *የእግዚአብሔር* ቀን ይመጣል፤
ብዝበዛሽንም በውስጥሽ ይካፈላሉ።
2 ኢየሩሳሌምን እንዲወጉ አሕዛብን ሁሉ
እሰበስባለሁ፤ ከተማዪቱ ትያዛለች፤ ቤቶች
ይበዘበዛሉ፤ ሴቶችም ይደፈራሉ፤ የከተማ
ዪቱ እኩሌታ ይማረካል፤ የሚቀረው ሕዝብ
ግን ከከተማዪቱ አይወሰድም።
3 *እግዚአብሔርም* በጦርነት ጊዜ እንደ
ሚዋጋ፣ እነዚያን አሕዛብ ሊወጋ ይወጣል።
4 በዚያን ቀን እግሮቹ ከኢየሩሳሌም በስተ
ምሥራቅ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ይቆማሉ፤
የደብረ ዘይት ተራራም ታላቅ ሸለቆን በመ
ሥራት የተራራውን እኩሌታ ወደ ሰሜን፣
እኩሌታውንም ወደ ደቡብ በማድረግ ምሥ
ራቅና ምዕራብ ሆኖ ለሁለት ይከፈላል፤
5 እናንተም በእግዚአብሔር ተራራ ሸለቆ
በኩል በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያን ዘመን
በምድር ትሸሻላችሁ፤ ሸለቆው እስከ አጸል
ይደርሳልና። በምድር በነውጥ[ኘ] ምክንያት
ሸሽታችሁ እንደ ነበረ ትሸሻላችሁ፤ ከዚያም
አምላኬ *እግዚአብሔር* ይመጣል፤ ቅዱሳኑም
ሁሉ አብረውት ይመጣሉ።
6 በዚያ ቀን በረዶ ውርጭና ብርሃን
አይኖርም። 7 ቀኑም የብርሃን ወይም የጨለ
ማ ጊዜ የሌለበት ልዩ ቀን ይሆናል፤ ያም
ቀን *በእግዚአብሔር* የታወቀ ቀን ይሆናል፤
ሲመሽም ብርሃን ይሆናል። 8 በዚያን ቀን
የሕይወት ውሃ ከኢየሩሳሌም ይፈልቃል፤
እኩሌታው ወደ ምሥራቁ ባሕር[ጦ]፣ እኩሌ
ታውም ወደ ምዕራቡ ባሕር[ጮ] ይፈሳል፤
ይህም በበጋና በክረምት ይሆናል።
9 *እግዚአብሔር* በምድር ሁሉ ላይ ይነ
ግሣል፤ በዚያን ቀን *እግዚአብሔር* አንድ፣
ስሙም አንድ ብቻ ይሆናል።
10 ምድር ሁሉ ከጌባ አንሥቶ በኢየሩሳ
ሌም ደቡብ እስካለችው ሬሞን ድረስ ተለ
ውጣ ደልዳላ ሜዳ ትሆናለች፤ ኢየሩሳሌም
ግን ከብንያም በር እስከ መጀመሪያው
በር፣ ከማእዘን በርና ከሐናንኤል ግንብ
እስከ ንጉሡ የወይን ጠጅ መጥመቂያ
ድረስ በዚያው በቦታዋ ላይ ከፍ እንዳለች
ትኖራለች። 11 የሰው መኖሪያም ትሆናለች፤
ከቶም ዳግመኛ አትፈርስም፤ ኢየሩሳሌም
ያለ ሥጋት በሰላም ትኖራለች።
12 *እግዚአብሔር* ኢየሩሳሌምን የወጓትን
አሕዛብ ሁሉ የሚመታበት መቅሠፍት ይህ
ነው፤ ገና በእግራቸው ቆመው ሳሉ ሥጋ
ቸው ይበሰበሳል፤ ዐይኖቻቸው በጕድጓዶቻ
ቸው ውስጥ እንዳሉ ይበሰብሳሉ፤ ምላሶቻቸ
ውም በአፎቻቸው ውስጥ እንዳሉ ይበሰብ
ሳሉ። 13 በዚያ ቀን *ከእግዚአብሔር* ዘንድ በሰዎች
ላይ ታላቅ ሽብር ይወርዳል፤ እያንዳንዱ
ሰው የባልንጀራውን እጅ ይይዛል፤ አንዱም
ሌላውን ይወጋዋል። 14 ይሁዳም ደግሞ ኢየሩ
ሳሌምን ይወጋል። በዙሪያው ያሉ የአሕዛብ
ሁሉ ሀብት፣ ብዙ ወርቅ፣ ብርና ልብስ
ይሰበሰባል። 15 ይህንኑ የሚመስል መቅሠ
ፍት ፈረሶችን፣ በቅሎዎችን ግመሎችንና
አህዮችን እንዲሁም በየሰፈሩ ያሉትን እንስሶች

14፥1 ኢሳ13፥6፤ 23፥18፤ኢል1፥15፤ ሚል4፥1
14፥2 ዘፍ34፥29፤ ኢሳ2፥3፤13፥6፤ ሰቆ5+11፤ሕዝ5፥8፤ ዘካ12፥3፤13፥8
14፥3 ኢሳ8፥9፤ ዘካ9፥14-15፤12፥9
14፥4 ዘፍ16፥31፤ ሕዝ11፥23
14፥5 ዘዳ33፥2፤ ኢሳ29፥6፤66፥15-16፤አሞ1፥1፤ ማቴ16፥27፤25፥31፤ ይሁ14
14፥6 ኢሳ13፥10፤ ኤር4፥23
14፥7 ኢሳ13፥10፤ 30፥26፤ኤር30፥7፤ ራእ21፥23-25፤22፥5
14፥8 ዘፍ8፥22፤ ኢሳ30፥25፤ ሕዝ47፥1-12፤ ኢል2፥20፤ ዮሐ7፥38፤ራእ22፥1-2
14፥9 ዘዳ6፥4፤ መዝ22፥28፤ 47፥7፤ኢሳ45፥24፤ አብ1፥21፤ዕን2፥14፤ ኤፌ4፥5-6፤ ራእ11፥15
14፥10 ኢሱ 15፥32፤1ነገ15፥22፤ 2ነገ14፥13፤ ነህ3፥1፤ኢሳ2፥2፤ ኤር20፥2፤30፥18፤ አሞ9፥11፤ዘካ12፥6
14፥11 መዝ 48፥8፤ሕዝ34፥25-28፤ ዘካ2፥4
14፥12 ቍ18፤ ዘሌ26፥16፤ዘዳ28፥22 ፤ኢዩ18፥13፤ ኢሳ 11፥4
14፥13 ዘፍ35፥5፤ መሳ7፥22፤ዘካ11፥6
14፥14 ኢሳ23፥18፤ ዘካ12፥2 14፥15 ቍ12

ኘ5 ወይም *ተራራዩ ሸለቆ ይርማል እስከ አጸል ይሰፋፋል። በርዕደ መሬት ባቢያ እንደ ተዘጋው ሁሉ ለወደፊቱም እንደዚያ ይሆናል*
ጦ8 ሙት ባሕር ነው ጮ8 ሜድትራኒያን ነው

13፥9፤ *ሕዝቤ ናቸው... እግዚአብሔር አምላካችን ነው ይላሉ፤* የ8፥8 ማብ ይመ። ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ነበራቸው ትክክለኛ የኪዳን ግንኙነት ይመለሳሉ (ሕዝ20፥30-44 ይመ)።

14፥2፤ *ኢየሩሳሌምን እንዲወጉ አሕዛብን ሁሉ፤* ቍ12 ይመ፤ እንዲሁም የ12፥3 ማብ ይመ።

14፥3፤ *በጦርነት ጊዜ፤* በቀይ ባሕር እንደሆነው ሁሉ (የዘፀ 14፥14ማብ ይመ) እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመታደግ ጣልቃ እን ደሚገባ የሚያመለክት ነው።

14፥4፤ *በደብረ ዘይት ተራራ፤* በብሉይ ኪዳን ይህ ስም የሚገኘው በዚህ ስፍራና በ2ሳሙ15፥30 ላይ ብቻ ነው። ምናል ባት ይህ ትንቢት በሐሥ1፥11-12 ላይ የተፈጸመውን ሊያመ ለክት ይችላል። *ምሥራቅ፤* ቤተ መቅደሱ ካለበት ተራራ ትይዩ ያለ ሲሆን ከፍታው 832 ሜትር ያህልና ቤተ መቅደሱ ካለበት ተራራ 60 ሜትር ያህል ከፍ ያለ ነው (ከሕዝ11፥23፤43፥12 ጋር ያነጻጽሩ)።

*14፥5፤* አጸል፤ ከኢየሩሳሌም በስተምሥራቅ የሚገኝ የቦታ ስም ሲሆን፣ ይህም የአዲሱ ሸለቆ ምሥራቃዊ ጫፍ ነው፤ ትክ ክለኛ ስፍራው ግን አይታወቅም። *ቅዱሳኑም፤* መላእክትንና አማ ኞችን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም፤ እነርሱም ጌታችን ሲመጣ ያጅቡታል (ከማቴ25፥31፤1ተሰ3፥13፤ይሁዳ14፤ራእ19፥14ጋር ያነጻጽሩ)።

14፥7፤ *ልዩ ቀን፤* የኢሳ60፥19-20 እና ማብ ይመ፤ እንዲ ሁም ከራእ21፥23-25፤22፥5 ጋር ያነጻጽሩ።

14፥8፤ *የሕይወት ውሃ... ይፈልቃል፤* ቃል በቃልና ትእ ምርታዊ ትርጒም ሊኖረው ይችላል (ከመዝ46፥4፤65፥9፤ኢሳ8፥6፤ ኤር2፥13፤ሕዝ47፥1-12፤ኢል3፥18፤ዮሐ4፥10-14፤7፥38፤ራእ22፥12 ጋር ያነጻጽሩ)።

14፥9፤ *እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ ይነግሣል፤* በቅ ዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ዐቢይ ሐሳብ ሆኖ በስፋት የቀረበ ትም ህርተ መለኮት ነው። *እግዚአብሔር...አንድ፤* ዘዳ6፥4፤ኢሳ43፥11 እና ማብ ይመ።

14፥10፤ *ከጌባ...ከኢየሩሳሌም፤* በስተ ሰሜን ሰሜን ምሥ ራቅ ዐሥር ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ እንዲሁም በይሁዳ ሰሜናዊ ድንበር ላይ የምትገኝ ናት 2ነገ23፥8። *ሬሞን፤* ዐይን ሬሞንም ይባላል (ነህ11፥29ይመ፤ ከኢሱ15፥32 ጋር ያነጻጽሩ)። በተራራ ማው አገር፣ ወደ አዜብ በሚወስደው ኰልኰለት ላይ፣ ከኢየሩ ሳሌም ደቡብ ደቡብ ምዕራብ 56 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ትገኛ ለች። *ደልዳላ ሜዳ፤* የዘዳ1፥1 ማብ ይመ። በኢየሩሳሌም ዙሪያ ያለው መሬት ሁሉ ይስተካከላል። *ኢየሩሳሌም...ከፍ እንዳለች ትኖራለች፤* የኢሳ2፥24 ማብ ይመ። ይኸውም በዝናና በማንኛ ውም ረገድ ሊሆን ይችላል። *ከብንያም በር መጀመሪያው በር ከሐናንኤል ግንብ፤* ምናልባት ሁሉም ከከተማዪቱ ቅጥር በስተ ሰሜን ምሥራቅ የሚገኙ ናቸው (ከኤር31፥38፤37፥12-13፤38፥7 ጋር ያነጻጽሩ)። *ከማእዘን በር፤* በሰሜን ምዕራብ ማእዘን ላይ ማለት ነው ከኤር31፥38 ጋር ያነጻጽሩ። *እስከ ንጉሥ የወይን ጠጅ መጥመቂያ፤* ከከተማዪቱ በስተደቡብ በኩል ማለት ነው፤ ስለዚህ ከተማዪቱን ሁሉ ያጠቃልላል።

14፥11፤ *መኖሪያም፤* 2፥4 ይመ። *ከቶም ዳግመኛ አትፈ ርስም፤* በምርኮ ወደ ባቢሎን እንደሄዱበት ዘመን አይሆንም ማለት ነው፤በባቢሎን ምርኮ ጊዜ እንደሆነው (ኢሳ43፥28እና ማብ ይመ)። *ኢየሩሳሌም ያለ ሥጋት...ትኖራለች፤* ኤር31፥40ይመ።

14፥12፤ *ኢየሩሳሌምን የወጓትን አሕዛብ ሁሉ፤* ቍ2 ይመ፤ እንዲሁም የ12፥3 ማብ ይመ።*መቅሠፍት፤* ኢሳ37፥36 እና ማብ ይመ።

14፥13፤ *ታላቅ ሽብር...አንዱም ሌላውን ይወጋዋል፤* የመሳ7፥22ማብ ይመ።

14፥14፤ *ብዙ ወርቅ፣ ብርና ልብስ ፤* በጦርነት የተገኘ ምርኮ ነው፤ ይህም የቍ1ን ሁኔታ ለውጦታል።

*14፥15፤* ይህ መቅሠፍት ሕዝቡ ለማምለጥ እንዳይጠ

ሁሉ ይመታል::
[16]ከዚያም ኢየሩሳሌምን ከወጓት አሕ
ዛብ ከሞት የተረፉት ሁሉ ለእግዚአብሔር
ጸባኦት ለመስገድና የዳስን በዓል ለማክበር
በየዓመቱ ይወጣሉ:: [17]የምድር ሕዝብ ሁሉ
ለንጉሡ፣ ለእግዚአብሔር ጸባኦት ሊሰግዱ
ወደ ኢየሩሳሌም የማይወጡ ከሆነ ዝናብ
አያገኙም:: [18]የግብፅም ሰዎች ወደዚያ ሳይ
ወጡ ቢቀሩ፣ ዝናብ አያገኙም፤ እግዚአብሔር
ወጥተው የዳስ በዓልን በማያከብሩ አሕዛብ
ላይ የሚያደርሰውን መቅሠፍት በእነርሱም
ላይ ያመጣል:: [19]የዳስን በዓል ወጥተው ለማ
ያከብሩ ግብፃውያንና አሕዛብ ሁሉ የተወ
ሰነው ቅጣት ይህ ነው::

14፥16 ዘፀ23፥16፤ 2ነገ19፥31፤መዝ 22፥29፤86፥9፤ኢሳ 19፥21፤60፥6-9፤ አብ1፥21፤ሚክ4፥2
14፥17 2ዜና 32፥23፤ኤር14፥4፤አ ሞ4፥7
14፥18 ቁ-12፤ዘፍ27፥29
14፥19 ዕዝ3፥4
14፥20 ዘፀ 39፥30፤ሕዝ46፥20፤ ዘካ9፥15
14፥21 ነህ8፥10፤11፥1፤ኤር3 1፥40፤ ሕዝ44፥9፤ዘካ9፥8፤ ሮሜ14፥6-7፤ 1ቆሮ10፥31

[20]በዚያ ቀን በፈረሶች ሻኩራ ላይ፣ "ቅዱስ
ለእግዚአብሔር" የሚል ጽሑፍ ይቀረጻል፤
በእግዚአብሔር ቤት ያሉ የማብሰያ ምን
ቸቶች ከመሠዊያው ፊት ለፊት እንዳሉ
ሳሕኖች የተቀደሱ ይሆናሉ:: [21]በኢየሩሳ
ሌምና በይሁዳ ያሉ ምንቸቶች ሁሉ ለእግ
ዚአብሔር ጸባኦት የተቀደሱ ይሆናሉ፤
መሥዋዕት ለማቅረብ የሚመጡ ሁሉ ምን
ቸቶቹን በመውሰድ ያበስሉባቸዋል፤ በዚያን
ቀን በእግዚአብሔር ጸባኦት ቤት ከእንግ
ዲህ ወዲያ ከነዓናዊ[a] አይገኝም::

[a]21 ወይም ነጋዴ እነዚህ ሕዝቦች በአብዛኛው በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሳይሆኑ አይቀሩም::

ቀምባቸው የጋማ ከብቶቹን ያጠፉቸዋል::

14፥16፤ ኢሳ2፥24 እና ማብ ይመ:: *የዳስን በዓል፣* የዘፀ 23፥16፤የመዝ81፥3 ማብ ይመ:: ይህ ከሦስቱ ታላላቅ በዓላት መካከል አንዱ ነው (ዘፀ23፥14-17ይመ)፤ ምናልባትም የዳስ በዓል የተመረጠው አሕዛብን እንዲወክል ነው፤ ምክንያቱም በዕብራ ይስጥ የዘመን አቈጣጠር የመጨረሻውና ትልቁ በዓል ስለሆነና ሌሎችንም በዓላት ሁሉ ስለሚያጠቃልል ነው (የሕዝ45፥25 ማብ ይመ):: ይህም ታላቅ የደስታ ጊዜ ነው ዘሌ23፥40፤ዘዳ16፥13-15፤ነህ8፥17):: ከዕዝራና ከነህምያ ዘመን ጀምሮ፤ "የእግዚአብሔርን የሕግ መጽሐፍ" ማንበብና ማስተማር የበዓላቱ ዋና ክፍል ሆነ (ነህ8፥18 ይመ፤ ከኢሳ 2፥3 ጋር ያነጻጽሩ):: ይህ በዓል ስለ እስራኤል ሕዝብ ተሐድሶና ለመጨረሻ ጊዜ ለደስታ መሰብሰብ እንዲሁም ስለ አሕዛብ መሰብሰብ የሚናገር ነው::

14፥17፤ *ዝናብ አያገኙም፣* ባለመታዘዝ ከሚደርሱት ርግማኖች መካከል ይህ አንዱ ነው (ዘዳ28፥22-24 ይመ፤ከዘካ9፥11-10፥1 ጋር ያነጻጽሩ)::

14፥20፤ *"ቅድስና ለእግዚአብሔር፣"* በወርቅ ጥፍጥፍ ላይ ተቀርጾ፣ በሊቀ ካህናቱ የራስ ጥምጥም ላይ (ዘፀ 28፥36-38) የሚደረግ ሲሆን፣ ይህም ሊቀ ካህናቱ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለየ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው (የ3፥5 ማብ ይመ):: እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው ዘላለማዊ ዐላማ እውን ይሆናል (ዘፀ 19፥6 እና ማብ ይመ)::

14፥21፤ *በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ያሉ ምንቸቶች ሁሉ የተቀደሱ፣* ኢል 3፥17 ይመ:: ተራ የሆኑ ነገሮች እንኳ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሲውሉ የተቀደሱ ይሆናሉ:: *ከነዓናዊ፣* ማንኛውም ግብረገባዊና መንፈሳዊ ንጽሕና የሌለውን ሰው የሚወክል ነው፤ ይህም ከተመረጠው የእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ያልተጨመረ ያልተቀላቀለ ማለት ነው (ከኢሳ35፥8፤ ከሕዝ 43፥7፤44፥9፤ ከራእ 21፥27 ጋር ያነጻጽሩ)::